# SIDAAMU DAGOOMU QOQQOWI MOOTIMMA AFFINI GAAZEEXA

# የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አፍኒ ጋዜጣ

# SIDAAMA NATIONAL REGIONAL STATE AFFINI GAZETA

| | | |
|---|---|---|
| 3[ki] Diro Kiiro 27<br><br>Hawaasa, Badheessa 12, 2015 M.D | Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Amaalete Mini Allaalshi Hundaanni Fulinoho<br><br>በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ፫ ዓመት ቁጥር ፳፯<br><br>ሀዋሳ፣ መጋቢት ፲፪ ቀን ፳፻፲፭ ዓ.ም |



**Amado**

**Lallawu Kiiro 27/2015**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Baadiyyete Baatto Gashshootinna Horoonsishshi Lallawa Qoola …..**

**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር ፳፯/፳፻፲፭**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ገጽ …**


**Lallawu Kiiro 27/2015**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Baadiyyete Baatto Gashshootinna Horoonsishshi Lallawa**

Baattote annimma qoosso mootimmannitanna dagannita ikkase Itophiyu Federaalete Dimokiraasete Rippabilike Bayriidi seeriranna Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Bayriidi seerira seerroonnihura,

Baattonna kalaqamu jiro gashshate qoqqowubbate uynoonni biilloonye loosu aana hosiisanna yannicha baattote gashshsooti amuraate diriirsa hasiissinohura,

**አዋጅ ቁጥር ፳፯/፳፻፲፭**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ**

የመሬት ባለቤትነት መብት የመንግሥትና የህዝብ መሆኑ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት እና በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሕገ መንግስት በመደንገጉ፣

መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን ለማስተዳደር ለክልሎች የተሰጠው ሥልጣን በሥራ ላይ ማዋል እና ዘመናዊ የመሬት አስተዳደር ሰርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣


**Mittu Waagi ….**
**ያንዱ ዋጋ**

AFFINI GAAZEEXI P.S.K …..
አፍኒ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ….
Web address: www.affinigazet.gov.et

Babbaxxitino qoqqowu baattote gari qooxeessubba kaima assine qoqqowunnita hegeraame baadiyyete baatto massagaancho mixonna worada beeqqaancho assatenni tittirsha baatto horoonsi’rate mixo fushshatenninna loosu aana hosiisatenni baatto jawa horo uytanno garinni horoonsi’rate hattono kalaqamu jiro hegeraamu garinni agaratenni dagganno ilamara saysa hasiissinohura,

Baadiyyete baatto taje isilanchimma agarino garinni tantanatenninna yannitte assatenni horoonsidhanno dagaranna mootimmate garunni iillitanno assate dandiisiissannota qoqqowunni kayse eeliidi gashshootu taqqi geeshsha dirritannota yannittenna lifixa baadiyyete baatto taje amuraate diriirsa hasiissinohura,

Meyaati, wolqa ajjinonsarinna qarraho reqecci yitinoti dagoomu bissa baattote amado annimmanni taalo horonsi’rate qoosso mitte hekko nookkiha buuxisiisa dandiinanni gede xawadonna mereersinoha loosu amuraate diriirsa hasiissinohura,

Lallawu kiiro 456/1997 quwa 17 /1/ garinni qoqqowubba uminsaha noo akata hedote giddo worino garinni seera fushshate biilloonye uynoonniha ikkasinni,

Qoqqowu Bayriidi Seeri quwa 48 cinaancho quwa 3 fidale (a) garinni aane nooha lallanboonni.

በተለያዩ የክልሉ የሥነ ምህዳር ቀጠናዎች ላይ ተመስርቶ የክልሉን ዘላቂ የገጠር መሬት መሪ ዕቅድና በወረዳ አሳታፊ ዝርዝር የመሬት አጠቃቀም ዕቅዶችን በማዉጣትና በመተግበር መሬትን ከፍተኛ ጠቀሜታ በሚሰጥ መልኩ ለመጠቀም እንዲሁም የተፈጥሮ ሀብቶችን በዘላቂነት በመጠበቅ ለመጭዉ ትዉልድ ማስተላለፍ በማስፈለጉ፣

የገጠር መሬት መረጃ ጥራቱን በጠበቀ መልኩ በማደራጀትና ወቅታዊ በማድረግ ለተጠቃሚው ህብረተሰብና ለመንግስት በአግባቡ ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል ከክልል እስከ ታችኛዉ የአስተዳደር ዕርከን የሚዘልቅ ዘመናዊና ቀልጣፋ የገጠር መሬት መረጃ ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

የሴቶች፣ አቅመ ደካሞችና ለችግር ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በመሬት ይዞታ ባለቤትነት እኩል የመጠቀም መብት ያለምንም ተጽዕኖ ማረጋገጥ እንዲቻል ግልጽና አሳታፊ የሆነ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

በአዋጅ ቁጥር 456/1997 አንቀጽ 17 /1/ መሰረት ክልሎች የራሳቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ሕግ የማውጣት ስልጣን የተሰጠ በመሆኑ፣

በክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፵፰ ንዑስ አንቀጽ ፫ ፊደል ተራ (ሀ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## Gafa Mite

## Xaphooma Woro

1. **Harancho Umo**

   Konne lallawa **"Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Baadiyyete Baatto Gashshootinna Horoonsishshi Lallawa Kiiro 27/2015 M.D"** yine xawisa dandiinanni.

2. **Tiro**

   Konni lallawi giddo qaalu eo wole tiro uysiissannoha ikka hoogguro:-

   1/ **"Qoqqowo"** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimmaati.

   2/ **"Biiro"** yaa Qoqqowu Irshunna Kalaqamu Jiro Latishshi Biirooti.

   3/ **"Baadiyyete Baatto"** yaa quchumu qoqqowi gobbaanni noo ayee baattooti.

   4/ **"Baadiyyete Baatto Gashshoote"** yaa baadiyyete baatto amado qoosso uynanni, wowe buuxisiinsanni, baattote jiro waaga bikkinanni, baattote horonsishshi mixo jeefinsanni, baattote horonsi'raano mereero ka'anno kipho tirranni, gadacho jeefinsanninna taje gamba assine tantanatenni fattallannitanna horonsi'raanote iillinshanni ha'rinshooti.

   5/ **"Baattote Horoonsishsha"** yaa baadiyyete baatto seekkine amadatenni hegeraame doogoonni manchi beetti babbaxitino horo afi'rate baattote aana assanno ayee assooteeti.

   6/**"Gawajjaancho Baattote Horoonsishsha"**

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር ፳፯/፳፻፲፭ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

   1/ **"ክልል"** ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነው፡፡

   2/ **"ቢሮ"** ማለት የክልሉ የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮ ነዉ፡፡

   3/ **"የገጠር መሬት"** ማለት ከከተማ ክልል ዉጪ ያለ ማንኛዉም መሬት ነዉ፡፡

   4/ **"የገጠር መሬት አስተዳደር"** ማለት የገጠር መሬት ይዞታ መብት የሚሰጥበት፣ ዋስትና የሚረጋገጥበት፣ የመሬት ሀብት ዋጋ የሚተመንበት፣ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ የሚተገበርበት፣ በመሬት ተጠቃሚዎች መካከል የሚነሱ ግጭቶች የሚፈቱበት፣ ግዴታዎች የሚተገበሩበት እና መረጃ በመሰብሰብ በማደራጀት የሚተነተንበትና ለተጠቃሚዎች የሚሰራጭበት ሂደት ነው፡፡

   5/ **"የመሬት አጠቃቀም"** ማለት የገጠር መሬትን በእንክብካቤ ይዞ ዘላቂነት ባለው መንገድ የሰው ልጅ የተለያዩ ጥቅሞችን ለማግኘት በመሬት ላይ የሚያደርገው ማንኛውም የተግባር

yaa baattonnita kalaqamu amado bikku aleenni horoonsi'ratenni baattote shaqqille woy qooxeessaho noo mu'ro woy dannaho nooha woy qooxeessa gawajjanno garinni horoonsi'rate

7/ **"Baadiyyete Baatto Horoonsishshi Mixo"** yaa baattote suude, miinjunna dagoomitte tajubba kaima assatenni baadiyyete baatto uytara dandiitanno babbaxxitino baattote horoonsishshi doorshubba mereero baattote gawajjamanna qooxeessu daafama kalaqqukkinni jawa miinju horo afisiissanno doorshubba gumullanninna loosu aana hosiinsanni hayyo woy amuraate ikkanna hayyite qarqaru latishshi mixo hanqafanno.

8/ **"Baattote Horoonsishshi Massagaancho Mixo"** yaa baattote horo gumaamenna sumuu yitinota hattono gawajjannoha baattote horoonsishsha hooltanno garinni qixxaabbino gobboomunna qoqqwu baattote horoonsishshi mixooti.

9/ **"Awuuto"**yaa qeedhichimmate iillitinokkirenna amanna annansa reyoote woy wolu korkaatinni hooggino ooso loossanno gede seerunni afamooshshe uynoonnisi kalaqamu manchooti.

10/ **"Baatto Loosi're Galinoha"** yaa qara woy uurrinshunni giwirinnu loosinni galannoha ayee mancho ikkanna giwirinnu investere dihanqafanno.

11/ **"Gama Wido Saada Ce"e Galinoha"** yaa qara galtinosi saada ceatenninna bikku deerrinni irshunni afi'nanni laalchi aana

ክንዋኔ ነው፡፡

6/ **"ጎጅ የመሬት አጠቃቀም"** ማለት የመሬትን ተፈጥሯዊ ይዘት ከመጠን በላይ በመጠቀም የመሬቱን ለምነት ወይም በዙሪያዉ ያሉ እጽዋትን ወይም ድንበርተኛዉን ወይም አካባቢዉን በሚጎዳ መልኩ መጠቀም ነዉ፡፡

7/ **"የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድ"** ማለት የመሬትን አካላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ የገጠር መሬት ሊሰጥ ከሚችለው የተለያዩ የመሬት አጠቃቀም አማራጮች መካከል የመሬት መጎሳቆልንና የአካባቢን ብክለት ሳያስከትሉ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚያስገኙት አማራጮች የሚወሰኑበትና ተግባራዊ የሚደረጉበት የአሠራር ዘዴ ወይም ስርዓት ሲሆን ስልታዊ የአካባቢ ልማት ዕቅዶችን ያጠቃልላል፡፡

8/ **"የመሬት አጠቃቀም መሪ እቅድ"** ማለት የመሬት ጥቅም አዋጭና ተስማሚ ብሎም ጎጂ የመሬት አጠቃቀምን በሚከላከል መልኩ የተዘጋጀ ሀገራዊና ክልላዊ የመሬት አጠቃቀም እቅድ ነው፡፡

9/ **"ሞግዚት"** ማለት ለአካለ መጠን ያልደረሱና እናትና አባታቸውን በሞት ወይም በሌላ ምክንያት ያጡ ልጆችን እንዲያሳድግ በህግ እውቅና የተሰጠው የተፈጥሮ ሰው ነው፡፡

10/ **"አርሶ አደር"** ማለት መደበኛ ወይም ቋሚ መተዳደሪያው የግብርና ሥራ የሆነ ማንኛውም ሰው ሲሆን የግብርና ኢንቬስተርን አያጠቃልልም፡፡

heeshshosi safi'rino baadiyyete dagoomi bisooti.

12/ **"Hallanyu Amado"** yaa baatto loosidhe galtinorinna gama wido saada ce'e galtinori woy konni lallawi garinni horoonsi'rate qoosso uynoonnisi bisi anga heedhe amadote buuxishshi xiinxote kaarta qixxeessineenna hallanyunni horoonsi'nanni baadiyyete baattooti.

13/ **"Dannawu Amado"** yaa baatto loosidhe galtannorinna gama wido saada ce'e galtannori dannawimmatenni amadde saada allaa'late, dubbohonna dagoomu owaantubbara horoonsidhanno baadiyyete baattooti.

14/ **"Mootimmate Amado"** yaa gobbate, qarqaru latishshinna lophpora yineenna federaaletenni hanafe eeli geeshsha heedhanno mootimmate amadonni qoqqonbe amandooninna albilliteno qoqqombara dandiinannita baadiyyete baatto xawisannoha ikkanna qoronboonni dubbu baatto, dubbu saadara qoronboonni baycho, paarkoota, mootimmate irshubba, shiilote baatto, garba, lagganna wolootano insa lawanno garinni amandoonnita hanqafanno.

15/ **"Xiinxo"** yaa mittu baychi aana heedhano dannunni bandoonninna amadote anni anga heedhanno baattooti.

16/ **"Xiinxo Leellishanno Kaarta"** yaa amadote annira mitte xiinxo aana noo qoossosi buuxanteenna amadosi hunda heedhanno xiinxo hiikko heedhannoro,

11/ **"ከፊል አርብቶ አደር"** ማለት በዋናነት ከብት በማርባት እና በተወሰነ ደረጃ ከእርሻ በሚገኝ ምርት ላይ ኑሮውን የመሠረተ የገጠር ህብረተሰብ ክፍል ነው፡፡

12/ **"የግል ይዞታ"** ማለት በአርሶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ወይም በዚህ አዋጅ መሰረት የመጠቀም መብት በተሰጠው አካል እጅ ሆኖ የይዞታ ማረጋገጫ የማሳ ካርታ ተዘጋጅቶለት በግል የሚጠቀሙበት የገጠር መሬት ነው፡፡

13/ **"የወል ይዞታ"** ማለት አርሶ አደሮች ወይም ከፊል አርብቶ አደሮች በወል ይዞታነት ለግጦሽ፣ ለደንና ለማህበራዊ አገልግሎቶች የሚጠቀሙበት የገጠር መሬት ነው፡፡

14/ **"የመንግሥት ይዞታ"** ማለት ለሀገር፣ ለአካባቢ ልማትና ዕድገት ተብሎ ከፌዴራል ጀምሮ በተዋረድ የሚገኙ በመንግሥት ይዞታነት ተከልሎ የተያዘና ወደፊት ሊከለል የሚችል የገጠር መሬትን የሚገልጽ ሲሆን፣ ጥብቅ የደን መሬቶችን፣ የዱር እንስሳት ጥብቅ ቦታዎች፣ ፓርኮች፤ የመንግሥት እርሻዎችን፣ የማዕድን መሬቶችን፣ ሃይቆችን፣ ወንዞችንና ሌሎችን በተመሳሳይ መልኩ የተያዙትን ያጠቃልላል፡፡

15/ **"ማሳ"** ማለት በአንድ ቦታ ላይ የሚገኝ በድንበር የተወሰነና በባለይዞታው እጅ የሚገኝ መሬት ነው፡፡

16/ **"የማሳ ጠቋሚ ካርታ"** ማለት ለባለይዞታው በአንድ ማሳ ላይ ያለው

xiinxote suude, hala'linyesinna woloota xaaddanno tajubba amadatenni baadiyyete baattonni horonsi'rate qoosso buuxisiisate hajo la'anno mootimmate uurrinshanni uynanniha ikke qoossonna gadacho amaddino seeru gari tajeeti.

17/ **"Baattote Maareekko"** yaa baadiyyete baatto bikkatenni heedhanno baycho, horonsi'rate qoosso, amadote annimma, shaqqillu deerranna hala'linyeseno lede wo'ma taje tajete aana maareekkate loosooti.

18/ **"Haja La'annosi Biso"** yaa qoqqowoho mittu mittunku gashshootu taqqira irshunna kalaqamu jiro latishshi tantano hunda tanatanantino taashshitinotanna hegeraame baadiyyete baatto gashshootinna horoonshu amuraati hala'lanno assannohanna loosono ha'ruunsate tantanantino loosu kifileeti.

19/ **"Xiinxo Leellishano Kaarta Uynanni Gara"** yaa raggete, beehaachunninna eltotenni afi'noonni amado maareekkatenninna bikkatenni tantanne qixxeessinoonni xiinxo leellishanno kaarta konni lallawinni biilloonye uynoonnisi bisinni buunxe uynanni ha'rinshooti.

20/ **"Baattote Taje Amuraate"** yaa baattote tajubba gamba assatenni, tittiratenni tajete maareekko giddo tantannenna garunni amadantanno gede assatenni babbaxxitino horaameeyye kifillara saysate amuraateeti.

21/ **"Bebbeeha"** yaa olluu giddo heedhanno gutunni woy mootimmatenni maareekkante



መብቱ ተረጋግጦ በይዞታዉ ስር የሚገኝ ማሳ የት እንደሚገኝ፣ የማሳውን ቅርፅ፣ ስፋቱንና ሌሎች ተያያዥ መረጃዎችን በመያዝ በገጠር መሬት የመጠቀምን መብት ለማረጋገጥ ጉዳዩ በሚመለከተው መንግሰታዊ ተቋም የሚሰጥ ሆኖ መብትና ግዴታን የያዘ ህጋዊ ሰነድ ነው፡፡

17/ **"የመሬት ምዝገባ"** ማለት የገጠር መሬትን በመለካት የሚገኝበትን ቦታ፣ የመጠቀም መብትን፣ ባለይዞታነትን፤ የለምነቱን ደረጃና ስፋቱን ጨምሮ የተሟላ መረጃ በመዝገብ ላይ የመመዝገብ ሥራ ነው፡፡

18/ **"አግባብ ያለዉ አካል"** ማለት በክልሉ በየአስተዳደር እርከኑ በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት አደረጃጀት ሥር የተደራጀ ፍትሃዊና ዘለቄታዊ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሥርዓት እንዲሰፍን የሚያደርግና ተግባሩንም ለመከታተል የተደራጀ የሥራ ክፍል ነው፡፡

19/ **"የማሳ ጠቋሚ ካርታ አሠጣጥ"** ማለት በዉርስ፣ በክፍፍል እና በስጦታ የተገኘን ይዞታ በመመዝገብና በመቀየስ ተደራጅቶ የተዘጋጀዉን የማሳ ጠቋሚ ካርታ በዚህ አዋጅ ሥልጣን በተሰጠዉ አካል ተረጋግጦ የሚሰጥበት ሂደት ነዉ፡፡

20/ **"የመሬት መረጃ ሥርዓት"** ማለት የመሬት መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በመተንተን፣ የመረጃ ቋት ውስጥ በማደራጀትና በአግባቡ እንዲያዙ በማድረግ ለተለያዩ ተጠቃሚ ክፍሎች የማስተላለፍ ሥርዓት ነው፡፡

amandantino baatto seeru garinninna qooxeessu dagoomi sumuume garinni baatto noonsakkirira woy dagate horora yineenna amadonsa agurtino mannira aate.

22/ **"Kira"** yaa baatto loosi're galinohu baattote amadosi wolu mannira bikkantino yanna giddo sheemaatunni ee danunni woy woxu horo adhanni owaantete aana hossanno gede assanno hayyooti

23/ **"Baattote Amado Anna"** yaa mitte baadiyyete baatto aana amadote qoosso noosi mancho, gamba yiino manna, dagooma, mootimmate biso, dagoomu uurrinsha woy seerunni mannimma noosi bisooti.

24/ **"Jiraamessa"** yaa baadiyyete baattoha investimentete fajjo fushshi're gibirinna industirete ledo xaadise handaara hakka luphi yino deerrira reekkitanno mixo qixxeessatenni jajjasi baadiyyete baatto aana fushshe miinju horo noosi loosira bobbahino ayee manchooti.

25/ **"Investimentetenni Horoonsi'rate Qoosso"** yaa mittu baadiyyete gashshooti qooxeessi giddo investimentete fajjo uynoonnisi manchi, gaamo woy uurrinsha su'minni maareekkame baadiyyete baatto sheemaatunni horoonsi'rate qoossooti.

26/ **"Horoonsi'rate Qoosso"** yaa konni lallawi garinni baatto horoonsi'rate, sayikki bisira raggetenni, eltotenni, kirunni woy soorrotenni saysate hattono amadosi aana laashshino jajja wowete amadisiise horoonsi'rate woy hirate qoossooti.

27/ **"Baattote Horoonsi'raancho"** yaa baadiyyete baatto horoonsi'rate qoosso

21/ **"ድልድል"** ማለት በቀበሌ ዉስጥ በሚገኙ በወል ወይም በመንግስት ተመዝግቦ የተያዘ መሬት በህግ አግባብና በአካባቢ ማህበረሰብ ይሁንታ መሰረት መሬት ለሌላቸው ወይም ለህዝብ ጥቅም ሲባል ይዞታቸዉን ለለቀቁ ሰዎች መስጠት ነው፡፡

22/ **"ኪራይ"** ማለት አርሶ አደር የመሬት ይዞታዉን ለሌላ ሰው ለተወሰነ የጊዜ ገደብ በውል ሰጥቶ የአይነት ወይም የገንዘብ ጥቅም እየተቀበለ አገልግሎት ላይ እንዲውል የሚያደርግበት ዘዴ ነው፡

23/ **"የመሬት ባለይዞታ"** ማለት በአንድ የገጠር መሬት ላይ የይዞታ መብት ያለው ግለሰብ፣ የሰዎች ስብስብ፣ ሕብረተሰብ፣ የመንግስት አካል፣ ማህበራዊ ተቋም ወይም ሌላ በሕግ ሰውነት ያለው አካል ነው፡፡

24/ **"ባለሀብት"** ማለት የገጠር መሬትን የኢንቨስትመንት ፈቃድ አውጥቶ ግብርናውን ከኢንዱስትሪው ጋር በማስተሳሰር ዘርፉን ወደ ላቀ ደረጃ የሚያሸጋግር ዕቅድ በመንደፍ መዋዕለ ነዋዩን በገጠር መሬት ላይ እያፈሰሰ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ባለው ሥራ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ነው፡፡

25/ **"በኢንቨስትመንት የመጠቀም መብት"** በአንድ በገጠር አስተዳደር አካባቢ ውስጥ የኢንቨስትመንት ፈቃድ በተሰጠው ግለሰብ፣ ቡድን ወይም ድርጅት ስም ተመዝግቦ የገጠር መሬትን በዉል የመጠቀም መብት ነው፡፡፡

26/ **"የመጠቀም መብት"** ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በመሬቱ የመገልገል፣ ለሶስተኛ ወገን በውርስ፣ በስጦታ፣ በኪራይ ወይም በልዉዉጥ የማስተላለፍ እንዲሁም በይዞታው ላይ ያፈራውን ንብረት ዋስትና በማስያዝ የመጠቀም ወይም የመሸጥ መብት ነው፡፡

27/ **"የመሬት ተጠቃሚ"** ማለት በገጠር መሬት የመጠቀም መብት የተሰጠው ማንኛውም ሰው ነው፡፡

28/ **"የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ"** ማለት በቀበሌ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጉዳዮችን በዚህ

uynoonnisi ayee manchooti.

28/ **“Baattote Gashshootinna Horoonsishshi Komite”** yaa olluu baattote gashshootinna horoonsishshi hajubba konni lallawira uynoonni biilloonyi garinni loosanno bisooti.

29/ **“Jajja”** yaa baatto agurranna baattote aana amadote anni kalaqi’rino ayee jajjaati.

30/ **“Uurrinshu Mu’ro”** yaa mittu diri aleenni keeshshitanno woy aantete dirrara laalcho uytanno murooti.

31/ **“Qoronboonni Dubbo”** yaa qooxeessahonna sirote jirora hattono batinye kalaqo agarooshshira yineenna mootimmatenninna dagoomunni qoqqomboonni woy qoqqombanni dubbooti.

32/ **“Guto Loosiinse Laalcho Beeqqa”** yaa amadote anni amadosi wolu bisira fajje xiinxosi loosiisatenna gide latisate ha’rinsho ikke gidu iillanno woyte sheematinsa garinni beeqqitanno ha’rinshooti.

33/ **“Olluu Teessaancho”** yaa qara teessosi mittu olliira assi’re hasiissanno owaantenna dagoomitte horosi hakkonni olliira afi’ranno ayee manchooti.

34/ **“Ila”** yaa mundeete ilaminoho woy lossi’noonniho.

35/ **“Maate”** yaa minaanna, minaama, ooso minaanninna minaama amanna anna hattono roduuwa hanqafanno.

36/ **“Mancho”** yaa kalaqamu mancho woy seerunni mannimate qoosso uynoonnisi bisooti.

አዋጅ በተሰጠዉ ስልጣን መሰረት የሚያከናዉን አካል ነዉ፡፡

29/ **“ንብረት”** ማለት ከመሬት በስተቀር በመሬቱ ላይ ባለይዞታዉ ያፈራዉ ማንኛውም ንብረት ነው፡፡

30/ **“ቋሚ ተክል”** ማለት ከአንድ አመታት በላይ የሚቆይ ወይም ለተከታታይ አመታት ምርት የሚሰጥ ተክል ነው፡፡

31/ **“ጥብቅ ደን”** ማለት ለአካባቢና ለዘረመል ሀብት እንዲሁም ለብዝሀ ህይወት ጥበቃ ሲባል በመንግስትና በማህበረሰብ የሚከለል ወይም የተከለለ ደን ነው፡፡

32/ **“የጋራ በማሳረስ ምርት መጋራት”** ማለት ባለይዞታዉ ይዞታዉን ለሌላ አካል በመፍቀድ ማሳዉን የማሳረስና የሰብል ምርት የማምረት ሂደት ሆኖ ሰብሉ ሲደርስ እንደ ዉላቸዉ የሚከፋፈሉበት ሂደት ነዉ፡፡

33/ **“የቀበሌ ነዋሪ”** ማለት መደበኛ መኖሪያውን በአንድ ቀበሌ አድርጎ መሰረታዊ አገልግሎቶችንና ማህበራዊ ጥቅሞቹን በዚያው ቀበሌ የሚያገኝ ማንኛውም ሰው ነው፡፡

34/ **“ልጅ”** ማለት በሥጋ የተወለደ ወይም ጉዲፈቻ ነው፡፡

35/ **“ቤተሰብ”** ማለት ባል፣ ሚስት፣ ልጆች፣ የባል እና የሚስት እናትና አባት እንዲሁም እህትና ወንድምን ይጨምራል፡፡

36/ **“ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

37/ በዚህ አዋጅ ውስጥ በአንድ ፆታ የተገለፀው ሌላኛውንም ፆታ ያካትታል፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ

37/ Konni lallawi giddo mitte kooteemmanni xawinsoonnihu wole kooteemmano hanqafanno.

3. **Jeefishshu Mamigeeshsha**

Kuni lallawi Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma giddo heedhanno ayee baadiyyete baatto aana jeefamannoha ikkanno.

## Gafa Lame

## Baadiyyete Baatto Gashshoote

## Cinaancho Gafa Mite

## Baadiyyete Baatto Afi’ranna Horoonsi’ra

4. **Amadote Dana**

Qoqqowu baadiyyete baatto aana noo amadote dani hallanyunniho, dannawunnihonna mootimmanniho.

5. **Baadiyyete Baatto Afi’ra**

1/ Gibirinnu loosinni galtanno baali baadiyyete baatto baatooshshiweelo afi’ratenna horonsi’rate qoosso noonsa.

2/ Dirisi 18 dironna hakkonni ale ikkinosihunna gibirinnu loosinni galannohu woy galate hasi’rannohu ayee qoqqowu teesaanchi baadiyyete baatto amadote annimmanni afi’ratenna horonsi’rate qoosso noosi.

3/ Konni quwi cinaanchu quwi (2) aana worroonnihu hee’rirono dirinsa 18 diro wo’minonsakkirinna annanna ama reyootenni hooggino qaaqquulli loosidhe heedhanno baatto awuutonsa widoonni woy riqiwaanonsa widoonni woy lossi’raanonsa widoonni qolte afi’rate qoosso noonsa.

4/ Gibirinnu loosira bobbaha hasidhanno meyaati baatto baatooshshiweelo afi’ratenna horoonsi’rate qoosso noose.

መንግስት በሚገኝ በማንኛውም የገጠር መሬት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የገጠር መሬት አስተዳደር

## ንዑስ ክፍል አንድ

## የገጠር መሬት ስለማግኘትና ስለመጠቀም

4. **የይዞታ ዓይነቶች**

በክልሉ የገጠር መሬት ላይ ያሉ የይዞታ አይነቶች የግል፣ የወል እና የመንግስት ናቸው፡፡

5. **የገጠር መሬት ስለማግኘት**

1/ በግብርና ስራ የሚተዳደሩ ሁሉ የገጠር መሬት በነጻ የማግኘትና የመጠቀም መብት አላቸው፡፡

2/ ዕድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነውና በግብርና ሥራ የሚተዳደር ወይም ለመተዳደር የሚፈልግ ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ የገጠር መሬት በይዞታ የማግኘትና የመጠቀም መብት አለው፡፡

3/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) የተደነገገው ቢኖርም ዕድሜያቸው 18 ዓመት ያልሞላቸው እና አባት እና እናታቸውን በሞት ያጡ ህፃናት የሚተዳደሩበት መሬት በሞግዚቶቻቸው ወይም በወኪሎቻቸዉ ወይም በአሳዳጊዎቻቸው አማካኝነት የማግኘት መብት አላቸው፡፡

4/ በግብርና ሥራ መሰማራት የምትፈልግ ሴት መሬት በነጻ የማግኘትና የመጠቀም መብት አላት፡፡

5/ በግብርና ሥራ መሰማራት የሚፈልጉ የገጠር ወጣቶች በየአካባቢው ካለው የወል ወይም የመንግሥት መሬት የማግኘትና የመጠቀም መብት ይኖራቸዋል፡፡

6/ ለስራ ዕድል ፈጠራ በማህበራት የተደራጁ

5/ Gibirinnu loosira bobbaha hasidhanno baadiyyete wedelli qarqaraho noo gutu woy mootimmate baattonni afi’ratenna horoonsi’rate qoosso heedhannonsa.

6/ Loosu kaayyo kalaqate maamarratenni tantanantino wedelli mootimmatenna dannawu baattonni hattono lattino laayyote baatto lendanna latisse horonsi’rate qoosso noonsa.

7/ Ayiddaanninna ayiddaama baattote amadonsanni taalo horoonsi’rate qoosso noonsa. Baxxitino sumuumme hoogguha ikkiro adhamate albaanni noonsa baatto gutu amadonsa ikkitanno.

8/ Ayiddaama woy mine gashshino meenti baattote amadonsanni horonsi’rate wo’ma qoosso noonsa.

9/ Baattote amado noonsa ayiddaanni woy ayiddaama wolu qooxeessira hee’ransa amadonsa horoonsi’rate qoossonsa dikissanno.

10/ Baatto loosidhe galtinorinna gama wido saada ce’e galtinori gutu horora ikkitannota yaano saada allaa’late, dagoomittete, budunna amma’note hajubbara budunna rosichu garinni horoonsidhanni keeshshitino amado horoonsi’rate qoosso noonsa.

11/ Geedhitinori, wolqa ajjinorinna bisu gawajjo noonsa qansooti baadiyyete baatto amado anna ikkatenna horoonsi’rate qoosso noonsa.

12/ Baadiyyete latishshira bobbaha hasidhanno hallanya dureeyye Federaaletenna Qoqqowu investementete poolisenna seerubba garinni baadiyyete baatto aana latisate qoosso heedhannonsa.

13/ Mootimma amadose hunda noo baadiyyete baatto amado hasiishshu garinni hallanyu amadooshshi widira soorritara dandiitanno. Tittirsha wodhotenni gumullanni.

14/ Baatto loosi’re galinohu qoosso xiiwannokki garinni mootimmaame, mootimmaame

ወጣቶች የመንግስትና የወል መሬቶችን ከለሙ ተፋሰሶች ጭምር አልምተው የመጠቀም መብት አላቸው፡፡

7/ ባልና ሚስት በይዞታቸው እኩል የመጠቀም መብት አላቸው፡፡ ከጋብቻ በፊት የነበራቸው ይዞታ ልዩ ስምምነት ከሌለ በስተቀር የጋራ ይዞታቸው ይሆናል፡፡

8/ እማወራ ወይም የቤተሰብ ኃላፊ ሴቶች በይዞታቸው የመጠቀም ሙሉ መብት አላቸው፡፡

9/ የመሬት ይዞታ ያላቸው ባል ወይም ሚስት በሌላ አካባቢ መኖራቸው በይዞታው የመጠቀም መብትን አያሳጣቸውም፡፡

10/ አርሶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለጋራ ጠቀሜታ የሚሆን ማለትም ለግጦሽ፣ ለማህበራዊ፣ ለባሕላዊና ለእምነት ጉዳዩች በባህልና ልማድ መሰረት ሲጠቀሙበት የነበረውን ይዞታ የመጠቀም መብት አላቸው፡፡

11/ አረጋዊያን፣ አቅመ ደካማና አካል ጉዳተኞ ዜጎች የገጠር መሬት ባለይዞታ የመሆንና የመጠቀም መብት አላቸው፡፡

12/ በገጠር ልማት ለመሰማራት የሚፈልጉ የግል ባለሃብቶች በፌዴራልና በክልል የኢንቨስትመንት ፖሊሲዎችና ህጎች መሠረት በገጠር መሬት ላይ የማልማት መብት ይኖራቸዋል፡፡

13/ መንግስት በይዞታዉ ሥር የሚገኙ የገጠር መሬት ይዞታዎች እንደአስፈላጊነቱ ወደ ግል ይዞታነት እንዲቀየሩ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል::

14/ የአርሶ አደሩን መብት በማይጋፋ መልኩ መንግስታዊ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ማህበራዊ ተቋማት ለዓላማቸዉ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የገጠር መሬት

ikkitinokki uurrinshubbanna dagoomitte uurrinshubba hexxonsara hasiisannoha ikke leelliro baadiyyete baatto afi'ratenna horoonsi'rate qoosso heedhannonsa. Tittirsha wodhotenni gumullanni.

15/ Konni quwira cinaancho quwa (1) kayse (5) geeshsha worroonnihu hee'rirono, baatto bebbeehate doogonni afi'rate dandiinannihu qooxeessaho bebbeehate ikkitanno baatto noota buunxironna konni lallawi garinni gibirinnu loosira horonsi'rate injiitannota ikkase buunxiro callaati.

6. **Baattote Amadonna Horoonsi'rate Qoosso Kaajjite Keeshshitanno Yanna**

1/ Baatto loosidhe galtinoriranna gama wido saada ce'e galtinorira amadonsa aana noonsa qoosso yannate bikki dinoote.

2/ Konni quwi aana cinaanchu quwi 1 aana worroonniri hee'rirono konni lallawi quwa 19 garinni amadonsa annimma aana noonsa qoosso kiantara dandiitanno.

3/ Baadiyyete baatto kirunni afidhino dureeyye latisse horoonsi'rate yanna bikki konni lallawi giddo worroonni garinni ikkanno.

4/ Loosu kaayyo kalaqate maamarunni tantanantino wedellira uynoonni baatto latise horoonsi'rate noonsa yanna bikki sumuummetenni gumullanni. Ikkeennano tini sumuumme ontu dirinni sa"a dinose.

5/ Ayee baattote amado daninna baattoote aanaanni noota kalaqamu jiro latishshunna horoonsi'rate gari yannate bikki qarqaru agarooshshi seera mereersinoha ikka noosi.

6/ Konni quwira cinaancho quwa (5)

የማግኘትና የመጠቀም መብት ይኖራቸዋል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

15/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (5) የተደነገገው ቢኖርም መሬት በድልድል ሊገኝ የሚችለዉ በአካባቢዉ ለድልድል የሚሆን መሬት መኖሩ ሲረጋገጥና በዚህ አዋጅ መሰረት ለግብርና ስራ ለመጠቀም የሚዉል መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነዉ፡፡

6. **የይዞታና የመጠቀም መብት ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ**

1/ አርሶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች በይዞታቸው ላይ ያላቸው መብት የጊዜ ገደብ የለውም፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገዉ ቢኖርም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 20 መሰረት በይዞታቸው ላይ ያላቸው መብት ሊገደብ ይችላል፡፡

3/ የገጠር መሬትን በኪራይ ያገኙ ባለሃብቶች አልምቶ የመጠቀሚያ ጊዜ ገደብ በዚህ አዋጅ በተደነገገዉ መሰረት ይሆናል፡፡

4/ ለስራ ዕድል ፈጠራ በማህበር ለተደራጁ ወጣቶች የተሰጠ መሬት አልምቶ የመጠቀሚያ ጊዜ በስምምነት ይወሰናል፤ ሆኖም ስምምነቱ ከ5 ዓመት መብለጥ የለበትም፡፡

5/ በማንኛውም የይዞታ ዓይነትና ገጸ-ምድር ላይ ያሉ የተፈጥሮ ሀብቶች የልማት እና የአጠቃቀም ሁኔታው ግዜ ገደብ የአካባቢ ጥበቃ ህግን ያማከለ መሆን አለበት፡፡

6/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የማዕድን ልማት ተጠቃሚዎች በገጠር መሬት የመጠቀም መብት በማዕድን ህግ መሠረት ይወሰናል፡፡

worroonnihu noowa hee’reenna shiillote latishshi horoonsi’raano baadiyyete baatto horoonsi’rate qoosso shiilote seeri garinni gumulamanno.

7. **Baadiyyete Baatto Amado Annira Baattosi Aana Noosi Qoosso**

1/ Baatto loosidhe galtinorinna gama wido saada ce’e galtinori amadonsa aana wo’ma qoosso noonsa.

2/ Amadote anni baadiyyete baatto horoonsi’rate, kirunni aate, guto loosi’ratenna guma beeqqate, horoonsi’rate qoossosi asalu wowera amadisiisate, raggetenni woy eltotenni woleho saysate, guto dureessu ledo latisate, qasiiso assine horoonsi’rate hattono wole baadiyyete baattonni soorri’rate qoosso hanqafanno.

3/ Amadote anni baadiyyete baatto horoonsi’rate qoosso amadisiisatenni afamooshshe afidhino faynaansete uurrinshanni liqii’ra dandaanno.

4/ Baadiyyete baatto kirunni afi’rino dureessi loosi’re afi’rino jajja seerunni uynoonnisi yanna giddo baattote amado anni ledo eino sheemaate amadisiisatenni afamooshshe afidhino faynansete uurrinshanni liqii’ra dandiitanno.

5/ Loosu kaayyo kalaqate maamarunni tantanantino wedelli sheemaatu garinni uynoonninsa yanna giddo baatto gawajjitukkinni horonsi’rate baattote aana kalaqidhino jajja hiratenni miinja kalaqi’rate qoosso noonsaha.

6/ Cinaancho quwi 5 seerroonnihu hee’rirono horoonsi’rate qoossonsa kayinni wolu bisira saysa didandiitanno.

**Cinaancho Gafa Lame**

**Baadiyyete Baatto Horoonsi’rate**

7. **የገጠር መሬት ባለይዞታ በመሬቱ ላይ ስለሚኖረው መብት**

1/ አርሶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች በይዞታቸው ላይ ሙሉ መብት አላቸው፡፡

2/ የይዞታ ባለቤት የገጠር መሬትን የመጠቀም፣ የማከራየት፣ በጋራ የማሳረስና ምርት የመጋራት፣ የመጠቀም መብቱን በዕዳ ዋስትና የማስያዝ፣ በውርስ ወይም በስጦታ የማስተላለፍ፣ በጋራ ከባለሀብት ጋር የማልማት፣ ኩታ ገጠም በማድረግ መጠቀም፣ እንዲሁም በሌላ የገጠር መሬት የመለወጥ መብትን ያጠቃልላል፡፡

3/ የይዞታ ባለቤት የገጠር መሬት የመጠቀም መብትን በማስያዝ ዕዉቅና ካለዉ የፋይናንስ ተቋም መበደር ይችላል፤

4/ የገጠር መሬትን በኪራይ ያገኘ ባለሃብት ያፈራዉን ንብረት በህግ በተሰጠዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ ከባለይዞታዉ ጋር የገባዉን ዉል በማስያዝ ዕዉቅና ካለዉ የፋይናንስ ተቋም መበደር ይችላል፤

5/ ለስራ ዕድል ፈጠራ በማህበር የተደራጁ ወጣቶች በዉሉ መሰረት በተሰጣቸዉ የጊዜ ገደብ መሬቱን ሳይጎዱ የመጠቀም በመሬቱ ላይ ያፈሩትን ሀብት በመሸጥ ካፒታል የመፍጠር መብት አላቸው፡፡

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 የተደነገገው ቢኖርም የመጠቀም መብታቸዉን ለሌላ አካል ማስተላለፍ አይችሉም፡፡

**ንዑስ ክፍል ሁለት**

**የገጠር መሬት የመጠቀም**

**መብትን ስለማረጋገጥ**

8. **የገጠር መሬትን ስለመለካት፣ ስለመመዝገብና የይዞታ ማረጋገጫ የማሳ ጠቋሚ ካርታ ስለመስጠት**

**Qoosso Buuxisa**

8. **Baadiyyete Baatto Bikka, Maareekkanna Xiinxo Leellishano Kaarta Aa**

1/ Hallanyunni, dannawunninna mootimmate amadonni amadantinoti ayee baadiyyete baatto yannite bikkote uduunnichinni haja la'annonsa bissanni bikkanteennanna maareekkanteenna xiinxo leellishano kaarta qixxeessinannise.

2/ Ayee hajo la'annosi bisinni qixxaawanno amadote buuxishshi xiinxo leellishanno kaarti baattote amado hala'linye, baattote amado anni tittirshu xawishsha hattono qoossonna gadachosi amaddinoha ikke su'misinni qixxaawanno.

3/ Hallanyunni, dannawunninna hattono mootimmate amadooshshi hunda noo baadiyyete baatto ayee baatto ledo faro xaaddannoro, deerrise hiittoohoro, may horora hossannoronna amadote annira may qoossonna gadacho noosiro, baatto horonsi'rate akatinna shaqqillu deerrase xawissanno taje mareekkante haja la'annosi bisi anga amadantanno gede assinanni.

4/ Xiinxo leellishanno kaarti amadote annira seeru tajeeti.

5/ Baatto ayiddaanniranna ayiddamara gutunnita ikkitinoha ikkiro lamunku su'ma amadinoha mitto xiinxo leellishanno kaarta qixxeessine uynanninsa.

6/ Baatto gutu amado annimmanni amadantinoha ikkiro xiinxo leellishano kaarti gutu amado annuwi su'minni qixxaawe amadote annuwa sumuu yituhu anga ofollanno.

1/ በግል፣ በወልና በመንግስት ይዞታነት የተያዘ ማንኛውም የገጠር መሬት በዘመናዊ የቅየሣ መሣሪያ አግባብ ባለዉ አካል ተቀይሶና ተመዝግቦ የማሳ ጠቋሚ ካርታ ይዘጋጅለታል፡፡

2/ ማንኛውም አግባብ ባለው አካል የሚዘጋጅ የይዞታ ማረጋገጫ የማሳ ጠቋሚ ካርታ የመሬቱን ይዞታ ስፋት፣ የባለይዞታ ዝርዝር መግለጫ፣ እንዲሁም መብትና ግዴታን የያዘ ሆኖ በባለይዞታዎች ስም ይዘጋጃል፡፡

3/ በግል፣ በወል እንዲሁም በመንግሥት ይዞታዎች ሥር ያለ የገጠር መሬት ከማን መሬት ጋር እንደሚዋሰን፣ ደረጃው ምን ዓይነት እንደሆነ፣ ለምን ጥቅም እንደሚውልና ባለይዞታው ምን መብትና ግዴታዎች እንዳሉበት፣ የመሬት አጠቃቀማቸውና የለምነት ደረጃቸውን የሚገልጽ መረጃ ተመዝግቦ በሚመለከተው አካል እንዲያዝ ይደረጋል፤

4/ የይዞታ ማረጋገጫ የማሳ ጠቋሚ ካርታ የባለይዞታው ህጋዊ ማስረጃ ነው፡፡

5/ መሬቱ የባልና የሚስት የጋራ ይዞታ ከሆነ የሁለቱንም ስም የያዘ አንድ የይዞታ ማረጋገጫ የማሳ ጠቋሚ ካርታ ተዘጋጅቶ ይሰጣቸዋል፡፡

6/ መሬቱ በጋራ ባለይዞታዎች የተያዘ ከሆነ የይዞታ ማረጋገጫ የማሳ ጠቋሚ ካርታዉ በጋራ ባለይዞታዎች ስም ተዘጋጅቶ ባለይዞታዎቹ በሚስማሙት እጅ ይቀመጣል፡፡

7/ በወል የተያዙ መሬቶችን በሚመለከት በአካባቢው ተጠቃሚዎች በቦታዉ ልዩ ስም ተመዝግቦና የይዞታ ማረጋገጫ የማሳ

7/ Dannawunni amadantino baatto lainohunni qarqaru horonsi'raanonni baychu addi su'minni maarreekkamenna xiinxo leellishanno kaarta qixxeessineenna olluu gashshooti borro mine ofollanno gede assinanni.

8/ Minensa annu nookki minu amuwira xiinxo leellishanno kaarta su'minsanni qixxeessine uynanninsa.

9/ Annunna amansa rewotenni baxxitinonsari dirinsa 18 diri woroonni noo ooso baattote amado annimmansa awuutonsa widoonni bikkinenna maareekkine oosote su'minni xiinxo leellishanno kaarta qixxeessine uynanninsa.

10/ Geedhitinorinna wolqa ajjinori dargaho leelte amadooshshensa maareekkisiisi'rate dandaa hoogguro seeru riqiwaanonsa widoonni bikkinenna maareekkine su'minsanni xiinxo leellishanno kaarta uynanninsa.

11/ Kirunni amadantino baadiyyete baatto baattote gashshootinna horonshi handaarinni maareekkama noose.

12/ Quchumu qoqqowi giddo heedhenni baadiyyete woraddanna olluubba widira su'mantinota loosidhe galtinori amado bikkinenna maareekkineenna xiinxo leellishano kaarta afi'rate dandiitanno. Tittirshu wodhotenni gumulamanno.

13/ Gama wido saada ce'e galannohu irshaho horoonsi'ranno baattora amadooshshu buuxishshi xiinxo leellishano kaarta uynannisi.

9. **Baadiyyete Baatto Bikkate, Maareekkatenna**

ጠቋሚ ካርታ ተዘጋጅቶ በቀበሌ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡

8/ በቤታቸዉ አባወራ ለሌላቸዉ እማወራዎች የይዞታ ማረጋገጫ የማሳ ጠቋሚ ካርታ በስማቸው ተዘጋጅቶ ይሰጣቸዋል፡፡

9/ ወላጆቻቸው በሞት የተለዩአቸው እድሜያቸው ከ 18 አመት በታች ያሉ ልጆች የመሬት ይዞታቸውን በሞግዚቶቻቸው አማካይነት ተለክቶና ተመዝግቦ በልጆቹ ስም የይዞታ ማረጋገጫ የማሳ ጠቋሚ ካርታ ተዘጋጅቶ ይሰጣቸዋል፡፡

10/ አረጋዊያንና አቅመ ደካሞች በቦታዉ ተገኝተዉ ይዞታቸዉን ማስመዝገብ ካልቻሉ በህጋዊ ተወካዮቻቸዉ አማካይነት ተቀይሶና ተመዝግቦ በስማቸዉ ይዞታ ማረጋገጫ የማሳ ጠቋሚ ካርታ ተዘጋጅቶ ይሰጣቸዋል፡፡

11/ በኪራይ የተያዘ የገጠር መሬት መመዝገብ አለበት፡፡

12/ በከተማ ክልል ሆነዉ በገጠር ወረዳዎችና ቀበሌዎች የተፈረጁ የአርሶ አደር ይዞታዎች በመለካትና በመመዝገብ የማሳ ጠቋሚ ካርታ ማግኘት ይችላሉ፤ ዝርዝሩ ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣው በደንብ ይወሰናል፡፡

13 ከፊል አርብቶ አደሩ ለእርሻ ለሚጠቀመዉ መሬት የይዞታ ማረጋገጫ የማሳ ጠቋሚ ካርታ ይሰጠዋል፡፡

9. **የገጠር መሬት ቅየሳ፣ ምዝገባና ይዞታ ማረጋገጥ ስርዓት**

1/ በክልሉ የሚከናወን የገጠር መሬት ቅየሳ ስራ ከአገር አቀፍ የመሬት መቆጣጠሪያ ነጥቦች ጋር መተሳሰር አለበት፡፡

**Amado Buuxisate Amuraate**

1/ Qoqqowu giddo assinannihu baadiyyete baatto bikkate loosi gobbate deerrinni noote baattote qorqorshi bixxillubba ledo xaada noosi.

2/ Qoqqowu giddo assinannihu baadiyyete baatto bikkate loosinna maareekkate ha'rinsho xiinxo kaima assinoha ikka hasiissanno.

## Cinaancho Gafa Sase

## Baadiyyete Baatto Horoonsi'rate Qoosso saysa

10. **Baadiyyete Baatto Amado Horoonsi'rate Qoosso Eltotenni Saysa.**

1/ Baadiyyete baatto amado horoonsi'rate qoosso noonsa amadote annuwi horoonsi'rate qoonsonsa konni lallawinna wolootu seerra garinni eltotenni saysa dandiitannohu maatete miillara callaati.

2/ Konni quwira cinaanco quwi (1) woro heedhurono baattote amado eltotenni saysa dandiinannihu umi deerimi ragi'rate qoosso noonsa ooso nookkiha ikkiro callaati.

3/ Baatto minanninna minaama woy wolootu mannooti gutu amado ikkituro minanninna minaama woy wolootu gutu amado afidhinnori sumuu yaa noonsa.

4/ Koonni quwira cinaanchu quwi (1) kayse (3) geeshsha worroonni balaxote ikkitubba wo'mituro nafa haa'nannihu elto borrotenni ikkite sheemaate maareekkatenna kaajjishate biilloonyi noo bisiwa shiqe maareekkamironna kaajjiro hattono qoosso saysate ha'rinshono woradu hajo la'annosi bisinni afamooshshe uynisirooti.

2/ በክልሉ ውስጥ የሚደረግ የገጠር መሬት ቅየሳና የምዝገባ ሂደት ማሳን መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡

## ንዑስ ክፍል ሶስት

## በገጠር መሬት የመጠቀም መብትን ስለ ማስተላለፍ

10. **በገጠር መሬት ይዞታ የመጠቀም መብትን በስጦታ ስለማስተላለፍ**

1/ በገጠር መሬት ይዞታ የመጠቀም መብት ያላቸው ባለይዞታዎች የመጠቀም መብታቸውን በዚህ አዋጅና በሌሎች ህጎች መሰረት በስጦታ ማስተላለፍ የሚችሉት ለቤተሰብ አባላት ብቻ ነው፡፡

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ይዞታ በስጦታ ማስተላለፍ የሚቻለው የመጀመሪያ ደረጃ የመውረስ መብት ያላቸው ልጆች የሌሉ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡

3/ መሬቱ የባልና ሚስት ወይም የሌሎች ሰዎች የጋራ ይዞታ ከሆነ ባልና ሚስት ወይም ሌሎች የጋራ ባለይዞታዎች መስማማት አለባቸው፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (3) የተቀመጡት ቅድመ ሁኔታዎች ቢሟሉም እንኳ ተቀባይነት የሚኖረው ስጦታው በጽሁፍ ሆኖ ዉልን ለመመዝገብና ለማጽደቅ ሥልጣን ወዳለዉ አካል ቀርቦ ሲመዘገብና ሲጸድቅ እንዲሁም የመብት ዝውውር ሂደቱም በወረዳው አግባብነት ባለው አካል እውቅና ሲሰጠው ነው፡፡

11. **በገጠር መሬት ይዞታ የመጠቀም መብትን**

11. **Baadiyyete Baatto Amado Horoonsi’rate Qoosso Raggetenni Saysa**

1/ Baadiyyete baatto horonsi’rate qoosso buuxantinnonsari loosidhe galtinorinna gama wido saada ce’e galtinori horoonsi’rate qoossonsa raggetenni saysa dandiitanno.

2/ Raggetenni sayinsanni amado seeru garita ikkitannohu yoote mine kaajjiturooti; ikkeennano woradaho hajo la’annosi bisiwa shiqe maareekkama noose.

3/ Konni lallawi quwi 17 garinni ragi’raanote mereero assinannihu raggete beehachi baattonniha miinjunna qooxeessu horo gawajjannokki garinni ikka hasiisanno.

12. **Kira**

1/ Baadiyyete baatto amado horoonsi’rate qoosso noonsari loosidhe galtinorinna gama wido saada ce’e galtinori horoonsi’rate qoossonsa gibirinu loosira bobbahate hasidhaanno loosidhe galtinoriranna hallanyu dureeyyera yannatenna uurrinshu mu’ro latishshira kirunni aa dandiitanno. Kiru yanna 25 diri geeshsha iillitara dandiitannota ikkite:-

a) Yannate mu’rora loosidhe galtinori loosidhe galtinorira kirunni uytannoha ikkiro 2 diri geeshsha hattono loosidhe galtinori dureeyyete kirunni uytanno woyte 5 diri geeshsha kiru yanna ikkanno.

**b)** Uurrinshate mu’rora loosidhe galtinori loosidhe galtinorira 10 diri geeshsha hattono loosidhe galtinori dureeyyete 25 diri geeshsha kiru yanna ikkanno.

**በውርስ ስለማስተላለፍ**

1/ በገጠር መሬት የመጠቀም መብት የተረጋገጠላቸዉ አርሶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች የመጠቀም መብታቸዉን በውርስ ሊያስተላልፉ ይችላሉ፡፡

2/ በዉርስ የሚተላለፈው ይዞታ ህጋዊ የሚሆነዉ በፍርድ ቤት ሲጸድቅ ነዉ፤ ሆኖም ለወረዳው አግባብነት ላለው አካል ቀርቦ መመዝገብ አለበት፡፡

3/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 መሰረት በወራሾች መካከል የሚደረገው የውርስ ክፍፍል የመሬቱን ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ጥቅም በማይጎዳ መልኩ ሊሆን ይገባል፡፡

12. **ኪራይ**

1/ በገጠር መሬት ይዞታ የመጠቀም መብት ያላቸው አርሶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች የመጠቀም መብታቸውን በግብርና ሥራ ለመሰማራት ለሚፈልጉ አርሶ አደሮችና የግል ባለሃብቶች ለዓመታዊና ቋሚ ሰብል ልማት ማከራየት ይችላሉ፡፡ የኪራይ ዘመኑ እስከ 25 ዓመት ሊደረስ የሚችል ሆኖ፡-

ሀ) ለዓመታዊ ሰብል አርሶ አደር ለአርሶ አደር የሚያከራይ ከሆነ እስከ 2 ዓመት እንዲሁም አርሶ አደር ለባለሀብት ሲያከራይ እስከ 5 ዓመት የኪራይ ዘመን ይሆናል፡፡

ለ) ለቋሚ ሰብል አርሶ አደር ለአርሶ አደር እስከ 10 ዓመት እንዲሁም አርሶ አደር ለባለሀብት ሲያከራይ እስከ 25 ዓመት የኪራይ ዘመን ይሆናል፡፡

2/ ማንኛዉም የኪራይ ውል ተቀባይነት የሚኖረው በጽሁፍ ተዘጋጅቶ ዉልን ለመመዝገብና ለማጽደቅ ሥልጣን ወዳለዉ አካል ቀርቦ

2/ Ayee kiru sheemaati haa'nanniha ikkannohu borrotenni qixxaawe sheemaate maareekkatenna kaajjishate biilloonyi noo bisiwa shiqe maareekkamironna kaajjiro hattono hajo la'annosi bisinni afamooshshe uynisirooti.

3/ Baattote amado kiruni adhinohu adhino yanna giddo horoonsi'rate qoosso sheemaate asaleho amadisiisa dandaanno; ikkeennano asaleho amadisiinsannihu amadote buuxishshi xiinxo leellishanno kaarta ikka dinosi.

4/ Baattote kiru sheemaate liqoote asalinni amadino bisi kirunni adhinohu asalesi baata hoogeenna sayikki bisira sayse uyro sayikki bisi horoonsi'rate dandaannohu wowete amandi barrinni hanafe 10 dirira calla ikkanno. Ikkeennano qara kiru sheemaati aana worroonni yanna aleenni ikka dinosi.

5/ Baadiyyete baatto kiru sheemaate e'nanni woyte baatto minanninna minaama woy wolootu mannooti gutu amado ikkituro minanninna minaama woy wolootu gutu amado afidhinnori sumuu yaa noonsa.

6/ Amadote kiri sheemaati kiru yanna gooffuro jajju kiiso xa'mo nookkiha woy sumuummetenni ka''anno; jajjasi kaysi're amado kirunni uynohura qola noosi.

7/ Konni quwira cinaanchu quwi (6) woro heedhurono xiinxote aana latisino laalchi horo aate 6 agani gatannosiha ikkiro kirunni adhinohu baattote amado annira ledote baatooshshe baate laalchu illeenna kaysi'ra dandaanoha ikkanna ayee korkaatinnino kira adhinohu 6 agani aleenni keeshsha didandaanno; Kayinnilla lamunku sheemaataano sumuu yituro sheemaatensa

ሲመዘገብና ሲጸድቅ እንዲሁም በወረዳው አግባብነት ባለው አካል እውቅና ሲሰጠው ነው፡፡

3/ የይዞታ ተከራይ በወሰደዉ የጊዜ ገደብ የመጠቀም መብት ዉል ለዕዳ ማስያዝ ይችላል፤ ሆኖም የዕዳ ማስያዣዉ የይዞታ ማረጋገጫ የማሳ ጠቋሚ ካርታ መሆን የለበትም፡፡

4/ የመሬት ኪራይ ዉል በብድር ዕዳ የያዘዉ አካል ተከራዩ እዳዉን መክፈል ባለመቻሉ ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ ቢሰጥ ሶስተኛ ወገን መጠቀም የሚችለዉ ለዋስትና ከተያዘበት ቀን አንስቶ ለ10 ዓመት ብቻ ይሆናል፡፡ ሆኖም በዋናው የኪራይ ውል ላይ ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ በላይ መሆን የለበትም፡፡

5/ የገጠር መሬት ኪራይ ውል በሚገባበት ጊዜ መሬቱ የባልና ሚስት ወይም የሌሎች ሰዎች የጋራ ይዞታ ከሆነ ባልና ሚስት ወይም ሌሎች የጋራ ባለይዞታዎች መስማማት አለባቸው፡፡

6/ የገጠር መሬት የኪራይ ዘመኑ ሲያበቃ ያለምንም የንብረት ካሳ ጥያቄ ወይም በስምምነት ንብረቱን አንስቶ ይዞታውን ለአከራይ መመለስ አለበት፡፡

7/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) ድንጋጌ ቢኖርም በማሳዉ ላይ የለማዉ ምርት ለጥቅም ለመድረስ እስከ 6 ወራት ጊዜ የሚቀረዉ ከሆነ ተከራዩ የቀሪዉን ጊዜ ተጨማሪ ኪራይ በመክፈል ምርቱ ደርሶ ማንሳት የሚችል ሲሆን በማንኛውም ምክንያት ተከራዩ ከ 6 ወር በላይ ሊቆይ አይችልም፤ ነገር ግን ሁለቱ ተዋዋዮች ከተስማሙ ዉላቸዉን በዚህ አዋጅ መሰረት እንደገና ማሳደስ ይችላሉ፡፡

## 13. ይዞታን ከባለሀብት ጋር በጋራ ስለማልማት

1/ በገጠር መሬት የመጠቀም መብት

የተረጋገጠለት ባለይዞታ በመሬቱ የመጠቀም

konni lallawi garinni wirro haaroonsi'ra dandiitanno.

13. **Amado Dureessu Ledo Guto Latisa**

1/ Baadiyyete baatto horoonsi'rate qoosso buuxantinosi amadote anni baatto horoonsi'rate qoosso amade dureessu ledo eanno sheemaati garinni gibirinnu looso loosara dandaanno.

2/ Baadiyyete baatto kiru sheemaate e'nanni woyte baatto minanninna minaama woy wolootu mannooti gutu amado ikkituro minanninna minaama woy wolootu gutu amado afidhinnori sumuu yaa noonsa.

3/ Konni quwira cinaancho quwi (1) garinni assinanni sheemaate haa'nannihu woradu hajo la'annosi bisiwa shiqe borreessamiro callaati.

14. **Gutunni Loosi'ratenni Laalcho Beeqqa**

1/ Ayno horoonsi'rate qoosso buuxatinosihu amadote anni amadosi wolu mannira sheemaatunni fajjatenni laalcho laashshinanni gede assatenni sheemaatu garinni laalcho beeqqa dandaanno.

2/ Baadiyyete baatto kiru sheemaate e'nanni woyte baatto minanninna minaama woy wolootu mannooti gutu amado ikkituro minanninna minaama woy wolootu gutu amado afidhinnori sumuu yaa noonsa.

3/ Konni quwi cinaanchu quwira (1) xawinsoonniha ayee laalcho beeqqate ha'rinsho yannara sayikki bissa ledo heedhanno laalchu kiisonna wole hajubba tidhantannohu sheemaatinsa garinni ikkanno.

4/ Laalcho beeqqatenni amado horonsi'rate qoosso 5 diri geeshsha calla ikkitanno.

15. **Amado Horoonsi'rate Qoosso Liqoote Wowera Amadisiisa.**

1/ Liqiissannohunna liqii'rannohu liqoote qolo yannara liqoo wo'ma woy gama qola hoogiro liqiissihu baatto amadate dandaanno yanna bikka xawadunni sheemaatinsa aana wora noonsa.

2/ Konni quwira cinaanchu quwi (1) aana

መብቱን ይዞ ከባለሀብት ጋር በሚገባው ውል መሰረት የግብርና ሥራ ሊሰራ ይችላል፡፡

2/ መሬቱ የባልና ሚስት ወይም የሌሎች ሰዎች የጋራ ይዞታ ከሆነ ባልና ሚስት ወይም ሌሎች የጋራ ባለይዞታዎች መስማማት አለባቸው፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚፈፀም ውል ተቀባይነት የሚኖረው በወረዳው ጉዳዩ በሚመለከተዉ አካል ቀርቦ ሲመዘገብ ብቻ ነዉ፡፡

14. **በጋራ በማሳረስ ምርትን መጋራት**

1/ ማንኛዉም የመጠቀም መብት የተረጋገጠለት ባለይዞታ ይዞታዉን ለሌላ ሰዉ በዉል በመፍቀድ ምርት እንዲመረት በማድረግ በዉሉ መሰረት ምርቱን መጋራት ይችላል፡፡

2/ መሬቱ የባልና ሚስት ወይም የሌሎች ሰዎች የጋራ ይዞታ ከሆነ ባልና ሚስት ወይም ሌሎች የጋራ ባለይዞታዎች መስማማት አለባቸው፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተዉ በማንኛዉም የምርት መጋራት ሂደት ወቅት ከሶስተኛ ወገኖች ጋር የሚኖር የካሳ እና ሌሎች ጉዳዮች የሚፈቱት በዉል ስምምነታቸው መሰረት ይሆናል፡፡

4/ በምርት መጋራት የይዞታ የመጠቀም መብት እስከ 5 ዓመት ብቻ ይሆናል፡፡

15. **በይዞታ የመጠቀም መብትን ለብድር ዋስትና ስለማስያዝ**

1/ አበዳሪና ተበዳሪ የብድር መመለሻ ጊዜንና ብድሩ በሙሉ ወይም በከፊል ባይመለስ አበዳሪ መሬቱን ሊይዝ የሚችልበትን የጊዜ ገደብ በግልጽ በውላቸው ላይ ማስቀመጥ አለባቸው፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ብድሩ ባለመመለሱ ምክንያት አበዳሪው በዋስትና የያዘውን መሬት የመጠቀም መብት ከ 10 ዓመት

worroonni woro noo gede heedheenna liqoo qola hoogate korkaatinni liqiissinohu wowete amadino baatto horoonsi'rate qoosso 10 diro roora didandiitanno. Ikkeennano qara kiru sheemaati aana worroonni yanna aleenni ikka dinosi.

3/ Konni quwira cinaanchu quwi (1) garinni assinanni sheemaate haa'nannihu woradu hajo la'anno bisi afamooshshe uyrooti.

16. **Amado Soorri'ra**

**1)** Ayno amadote anni amadosi qoqqowu giddo noo wole amado anni baatto ledo soorri'ra dandaannoha ikke ayee amadote anni:-

**a)** Olluu giddo noosi xiinxo wolu amadote anni xiinxo ledo,

**b)** Wolu ollii giddo noosi xiinxo wolu amadote anni xiinxo ledo,

**c)** Wolu woradira noo ollii giddo noosi xiinxo wolu woradira noo ollii amadote anni xiinxo ledo soori'ra dandaanno. Tittirsha wodhotenni gumullanni.

2/ Ayee soorri'rate sheemaati woradu hajo la'annosi bisinni afamooshshe uynasira hasiisanno.

3/ Baadiyyete baatto amado woy xiinxo soorro ha'rinsho minanninna minaama woy wolootu gutu amado ikkituro minanninna minaama woy wolootu gutu amadote annuwi gutu fajjo aana kaima assitinota ikka noose.

17. **Amado Qasiiso Assa**

1/ Manaadda xiinxo latishshaho injaabbinnota ikkitanno gede amadote annuwi amadonsa qasiiso assitara dandiitanno.

2/ Baadiyyete baatto amado woy xiinxo qasiiso assinanni woyte amado minanninna minaama woy wolootu mannooti gutu amado ikkituro minanninna minaama woy wolootu gutu amadote annuwi gutu fajjo aana kaima assinoha ikka noosi.

3/ Ayee amadono qasiiso assate sheemaate

ሊበልጥ አይችልም፡፡ ሆኖም በዋናው የኪራይ ውል ላይ ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ በላይ መሆን የለበትም፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚፈፀም ውል ተቀባይነት የሚኖረው በወረዳው አግባብነት ባለው አካል እውቅና ሲሰጠው ነዉ፡፡

16. **ይዞታን ስለመለዋወጥ**

1) ማንኛውም ባለይዞታ ይዞታውን በክልል ዉስጥ ካለዉ ከሌላ ባለይዞታ መሬት ጋር መለዋወጥ የሚችል ሆኖ ማንኛውም ባለይዞታ:-

ሀ) በቀበሌዉ ውስጥ ያለውን ማሳ ከሌላ ባለይዞታ ማሳ ጋር፣

ለ) በሌላ ቀበሌ ውስጥ ያለውን ማሳ ከሌላ ቀበሌ ባለይዞታ ማሳ ጋር፣

ሐ) በሌላ ወረዳ ባለዉ ቀበሌ ውስጥ ያለውን ማሳ በሌላ ወረዳ ቀበሌ ውስጥ ካለ ባለይዞታ ማሳ ጋር መለዋወጥ ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

2/ ማንኛውም የልውውጥ ውል በወረዳዉ አግባብነት ባለው አካል እውቅና ሊሰጠው ይገባል፡፡

3/ የገጠር መሬት ይዞታ ወይም ማሳ ልውውጥ ሂደት የባልና የሚስት ወይም የሌሎች ባለይዞታዎች የጋራ ይዞታ ከሆነ ልውውጡ የባልና የሚስት ወይም የሌሎች ባለይዞታዎች የጋራ ፈቃድ ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፡፡

17. **ይዞታን ኩታ ገጠም ማድረግ**

1/ አነስተኛ ማሳዎች ለልማት አመቺ እንዲሆኑ ባለይዞታዎች ይዞታቸውን ኩታ ገጠም ለማድረግ ይችላሉ፡፡

2/ የገጠር መሬት ይዞታ ወይም ማሳ ኩታ ገጠም እንዲሆን ሲደረግ ይዞታው የባልና የሚስት ወይም የሌሎች ባለይዞታዎች የጋራ ይዞታ ከሆነ ባልና ሚስት ወይም ሌሎች ባለይዞታዎች ፈቃድ ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፡፡

3/ ማንኛውም ይዞታን ኩታ ገጠም የማድረግ

haa'nannihu woradu hajo la'annosi bisinni afamooshshe uynirooti.

**Cinaancho Gafa Shoole**

18. **Baadiyyete Baatto Bikka Gumula**

1/ Konni albaanni noohu xeenunnino ikko gorsunni latannohu mitte maate amado hala'linyi noo gede hee'reenna albillicho hee'rannohu amadote bikki:

a) Xeenunni latannoha ikkiro shiimiidihu amadote bikki 0.25 hekitaare woroonni ikka dinosi,

b) Moottimmate fulonni loosame loosidhe galtinoriranna gama wido saada ce'e galtinorira uynannita gorsu baatto ikkituro bikkise qooxxeessu akati garinni ikkanno.

c) Konni quwira cinaancho quwa a nna b hunda worroonnihu hee'rirono minaanninna minaama tidhamanno woyte assinanni baattote amado beehache dila''anno.

**Cinaancho Gafa Onte**

**Amado Horonsi'rate Qoosso Hoonganninna Taashshinanni Gara**

19. **So'rotenni Jeefinsoonni Amado Buuxate Looso Taashshinanni Gara**

1/ Amadote buuxishshi xiinxote kaarta ayee bisirano doogimale aa dihasiissanno.

ውል ተቀባይነት የሚኖረው በወረዳው አግባብነት ባለው አካል እውቅና ሲሰጠው ነዉ፡፡

**ንዑስ ክፍል አራት**

18. **የገጠር መሬት የይዞታ መጠን ስለመወሰን**

1/ ቀደም ሲል የነበረው በዝናብም ሆነ በመስኖ የሚለማ የአንድ ቤተሰብ የመሬት ይዞታ ስፋት እንደተጠበቀ ሆኖ ወደፊት የሚኖረዉ የይዞታ መጠን፡-

ሀ) በዝናብ የሚለማ ከሆነ አነስተኛ የይዞታ መጠን 0.25 ሄክታር በታች መሆን የለበትም፡፡

ለ) በመንግሥት ወጪ ተሠርቶ ለአርሶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች የሚሰጥ የመስኖ መሬት ከሆነ መጠኑ እንደየ አካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ይሆናል፡፡

ሐ) በዚህ አንቀጽ ሀ እና ለ ሥር የተደነገገዉ ብኖርም ባልና ሚስት ፍቺ በሚፈጸሙበት ጊዜ የሚያደርጉትን የመሬት ይዞታ ክፍፍል አይመለከትም፡፡

**ንዑስ ክፍል አምስት**

**የይዞታ የመጠቀም መብት ስለሚታጣበትና ስለሚታረምበት ሁኔታ**

19. **በስህተት የተፈጸመ የይዞታ ማረጋገጥ ተግባር ስለሚታረምበት ሁኔታ**

1/ የይዞታ ማረጋገጫ የማሳ ጠቋሚ ካርታ ለማንኛዉም አካል አግባብ ባልሆነ መንገድ መሰጠት የለበትም፡፡

2/ Konni quwi cinaanchu quwa (1) worroonnihu noo gede hee’reenna amadote qoosso doogimale uynoonniha ikkiro konni lallawinni biilloonye uynoonni uurrinsha buuxxe taashsha dandiitanno.

20. **Baadiyyete Baatto Amadotenna Horonsi’rate Qoosso Hoonganni Gara**

1/ Baadiyyete baatto horoonsi’rate qoosso afidhinnori hallanyu, dannawunna mootimmate amado annuwi aantino korkaatubbanni, doogonninna akatubbanni amado horoonsi’rate qoosso hooggara dandiitanno:

a) Baatto dagate horora hansanni woyte Qoqqowu Gashshooti Amaale Mini woy riqiwo uynoonnisi bisi kiisote seeri garinni taaltino kiiso balaxxe baatatenni haa’riro,

b) Dannawu, hallanyunna mootimmate amado seeru gobbaanni ikkino garinni xiinxo leellishanno kaarta afi’noonniha ikkironna seeru gobbaanni ikkasi hajo la’annosi bisinni buunxiro,

c) Amado buuxisiisate looso loonsoonikki basera baatto horratenninna seeru gobbaanni ikkitino doogoni amaddino bissa seeru gobbaanni ikkansa qoqqowu giddo noo mitu mittunku gashshooti taqqira noo gashshootu bissanni buunxiro,

d) Baattote amado qoosso umisi fajjonni aguriro,

e) Gobbaaydi gobba qansichimma afi’ratenni,

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የይዞታ መብት አግባብ ባልሆነ መንገድ ተሰጥቶ ከተገኘ በዚህ አዋጅ ስልጣን የተሰጠዉ ተቋም አጣርቶ ማረም ይችላል፡፡

20. **የገጠር መሬት የይዞታና የመጠቀም መብት የሚታጣባቸው ሁኔታዎች**

1/ በገጠር መሬት የመጠቀም መብት የተረጋገጠላቸዉ የግል፣ የወልና የመንግስት ባለይዞታዎች በሚከተሉት ምክንያቶች፣ መንገዶችና ሁኔታዎች በይዞታ የመጠቀም መብታቸዉን ሊያጡ ይችላሉ፡-

ሀ) መሬቱ ለህዝብ ጥቅም ሲፈለግ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ወይም ዉክልና የተሰጠዉ አካል በካሳ ህግ መሰረት ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ በመክፈል ሲወሰድ፣

ለ) የወል፣ የግልና የመንግስት ይዞታዎች በህገወጥ የይዞታ ማረጋገጫ የማሳ ጠቋሚ ካርታ አማካይነት ይዞታዉን ያገኘ ከሆነና ህገወጥነቱ አግባብነት ባለው አካል ከተረጋገጠ፣

ሐ) የይዞታ ማረጋገጥ ተግባር ባልተካሄደባቸዉ ቦታዎች መሬትን በወረራና በህገወጥ መንገድ የያዙ አካላት ህገወጥ መሆናቸዉ በክልሉ ዉስጥ በየአስተዳደር እርከኑ ባሉ የአስተዳደር አካላት ሲረጋገጥ፣

መ) የመሬት ይዞታ መብቱን በራሱ ፍቃድ ሲተው፣

ሠ) የውጭ አገር ዜግነት በማግኘት፣

f) Saadate hayissora horoonsi’nanni baatto agurranna ikkadu korkaati nookkiha xeenunni lattanno baatto aantetenni 3 diri aleenni woy gorsunni lattanno baatto aantetenni 2 diri aleenni horote aana hosiisinokki woy mulla gashshino amadote anni qoossosi hoogara dandaanno. Tittirsha wodhotenni gumullanni.

**Gafa Sase**

**Baattote Horoonsishshi Mixonna Qorqorsha**

**Cinaancho Gafa Mite**

**Baattote Horoonsishshi Mixo Qixxaawonna Looso**

21. **Baattote Horoonsishshi Masagaancho Mixo Qixxeessa**
   1/ Qoqqowu baattote horonsishshi mixo qoqqowu akati gara hedote wortinota ikkite gobboomu baattote horonshi massagaancho mixo ledo sumuu yitanno garinni qoqqowu mootimmanni qixxaabbanno; loosantanno. Loonsanni garano wodhotenni gumullanni.
   2/ Baadiyyete baatto lattissannori, horoonsidhanorinna qorqorsha assittano bissa qinaabbe loosatenna qoqqowu baatto horoonsishshi masagaancho mixo qixxaawonna loosu aana hossanno gede kaa’lamate yawo noonsa.
   3/ Qoqqowunniti baadiyete baatto masagaancho mixo Qoqqowu Amaale Mininni kaaja noose.

ረ) ለእንስሳት ሳር ከሚጠቀሙበት መሬት በስተቀር ያለበቂ ምክንያት በዝናብ የሚለማ ይዞታውን በተከታታይ ከ3 ዓመት በላይ ወይም በመስኖ የሚለማ መሬት ከ2 ዓመት በላይ በጥቅም ላይ ያላዋለ ወይም ጾም ያሳደረ ባለይዞታ የመጠቀም መብቱን ሊያጣ ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

**ክፍል ሶስት**

**የመሬት አጠቃቀም ዕቅድና ቁጥጥር**

**ንዑስ ክፍል አንድ**

**የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ዝግጅት እና ትግበራ**

21. **የመሬት አጠቃቀም መሪ ዕቅድ ስለማዘጋጀት**
   1/ የክልሉ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ የክልሉን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ ሆኖ ከአገሪቱ የመሬት አጠቃቀም መሪ ዕቅድ ጋር በተጣጣመ መልኩ በክልሉ መንግስት ይዘጋጃል፣ ይተገበራል፡፡ አተገባበሩ በደንብ ይወሰናል፡፡
   2/ የገጠር መሬትን የሚያለሙ፣ የሚጠቀሙና የሚቆጣጠሩ አካላት ተቀናጅተዉ የመስራትና ለክልላዊ የመሬት አጠቃቀም መሪ ዕቅድ ዝግጅትና ተግባራዊነት ትብብር የማድረግ ኃላፊነት አለባቸዉ፡፡
   3/ የክልሉ የገጠር መሬት መሪ ዕቅድ በክልሉ ምክር ቤት መጽደቅ ይኖርበታል፡፡

22. **አሳታፊ አካባቢያዊ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ስለማዘጋጀት**

22. **Mereersitino Qooxeessu Baattote Horoonsishshi Mixo Qixxeessa**

1/ Qoqqowu hajo la'annosi bisi qoqqowoho heedhanno woradda qoqqowu baattote horonsishshi mixo loosi ledo sumuu yitinotanna kibbantannokki garinni woradu akati garinni jeefantannota woradu qooxeessa mereersitino baattote horonsishshi mixo heedhannonsa gede qineessanno.

2/ Qoqqowu giddo heedhano olluubba mereersitino olluu baattote horonsishshi mixo qixxeessa noonsa. Qixxaabbino mixo woradu amaalete minini kaaja noose.

3/ Konni quwi cinaancho quwi (2) woro heedhurono gama wido saada ce'e galtinori saada alaa'late horonsidhano qooxeessubbara baattote horonsishshi mixo baxxino garinni qixxeessa dandiinanni.

4/ Olluunnita mereersitino baadiyyete baatto horoonsishshi mixo qixxeessate tekinikete looso aliidimmatenni masaggano baattote horoonsishshi mixo tekinikete komite baalante woraddara uurritanno.

5/ Olluu deerrinni mixo ogeeyyete ledo halamatenni loossannonna gawajjaancho baattote horoonsishshi aana qorqorsha assitanno babbaxxitino dagoomu kifilenni gamba yitanno miilla noose komite baalante olluubbara uurrinseenna baattote gashshootinna horoonsishshi kifile ledo loossanno.

6/ Olluu mereersitino baadiyyete baatto horonsishshi mixo gooffuhu gedensaanni baatto horoonsi'ranohura xiinxote aani baattote horoonsishshi mixo qixxeessine amadote

1/ የክልሉ አግባብነት ያለው አካል በክልሉ የሚገኙ ወረዳዎች፣ ከክልሉ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ትግበራ ጋር በተጣጣመና በማይጋጭ መልኩ እንደ ወረዳዉ ነባራዊ ሁኔታ የሚፈጸም የወረዳ አካባቢያዊ አሳታፊ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ እንዲኖራቸዉ ያስተባብራል፡፡

2/ በክልሉ ያሉ ቀበሌዎች አሳታፊ የቀበሌ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ማዘጋጀት አለባቸዉ፡፡ የተዘጋጀው ዕቅድ በወረዳ ምክር ቤት መጽደቅ ይኖርበታል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም ከፊል አርብቶ አደሩ ለግጦሽ በሚጠቀምባቸው አካባቢዎች የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ በተመለከተ በተለየ ሁኔታ ሊዘጋጅ ይችላል፡፡

4/ የቀበሌ አሳታፊ የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድ ለማዘጋጀት የቴክኒክ ስራዉን በበላይነት የሚመራ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ የቴክኒክ ኮሚቴ በሁሉም ወረዳዎች ይቋቋማል፡፡

5/ በቀበሌ ደረጃ ዕቅዱን ከባለሙያዎች ጋር በመተባበር የሚሠራና ጎጂ የመሬት አጠቃቀም ላይ ቁጥጥር የሚያደርግ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍል የተዉጣጣ አባላት ያሉበት ኮሚቴ በሁሉም ቀበሌዎች ተቋቁሞ ከመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ክፍል ጋር ይሰራል፡፡

6/ የቀበሌ አሳታፊ የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድ ከተጠናቀቀ በኋላ ለመሬቱ ተጠቃሚ የማሳ ላይ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ተዘጋጅቶ ከይዞታ ማረጋገጫ የማሳ ጠቋሚ ካርታ በተጨማሪነት ይሰጠዋል፡፡

7/ የወል መሬቶች የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ በጋራ ተጠቃሚዎች ወይም በቀበሌ አስተዳደር ስም ተዘጋጅቶ ከወል ይዞታ ማረጋገጫ የማሳ ጠቋሚ ካርታ

buuxishshi xiinxo leellishshanno kaarti aana lende uynannisi.

7/ Dannawu baatto baattote horoonsishshi mixo gutu horoonsii'raano woy olluu gashshooti su'minni qixxeessine dannawu amado buuxishshi xiinxo leellishshanno kaarti aana lende uynanni.

8/ Woradu amaale mininni kaaajitinota olluunna woradu mereersitino baattote horoonsishshi mixo woradaho dagoomu kifillanna la'anonsa uurrinshubba ayirrissanna jeefisa noonsa.

9/ Baalante olluubbara heedhanno dagoomu kifilla konne lallawa ayirrisino garinninna lallawu garinni uurritino tekinikete komitenni irkisantanni baatto agaratenna agarate dandiisiisannoha qooxeessu akati garinni jefamanno assoote loosu aana hosiisa hasiissannonsa.

23. **Way Eelanno Baatto Horoonsishsha**

1/ Way eelanno baattonni waa darre fushshate looso loonsikkinni agarante kalaqamu qooxeessiranna batinye lubbuwate agarooshshi owaantera hosa hasiissanno.

2/ Yannate geeshsha way eelanno baatto qooxeessu akata hedote giddo wortinota dagoomite miinjunna "bayo-fizikaalete" xiinxallo kaima assitinota mereersitino baattote horoonsishshi mixo aana worroonni hexxora hosa hasiissannose.

3/ Lowo yannara waa amaddanno baatto aana way bikka soorrannore ayee loosono loosa hoolloonnite.

4/ Waa amaddanno baatto aaninni hayisso mide

በተጨማሪነት ይሰጣል፡፡

8/ በወረዳዉ ምክር ቤት የጸደቀዉን የቀበሌና የወረዳ አሳታፊ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ የወረዳዉ የህብረተሰብ ክፍሎችና የሚመለከታቸዉ ተቋማት ማክበርና መፈጸም አለባቸዉ፡፡

9/ በሁሉም ቀበሌዎች የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ይህን አዋጅ ባከበረ መልኩ እና በዚህ አዋጅ መሰረት በተቋቋሙ የቴክኒክ ኮሚቴ እየተደገፉ መሬቱን ለመንከባከብና ለመጠበቅ የሚያስችል እንደ አካባቢያቸዉ ተጨባጭ ሁኔታ የሚፈጸም አሰራር መተግበር አለባቸዉ፡፡

23.**የዉሃ አዘል መሬቶች አጠቃቀም**

1/ ዉሃ የሚተኛባቸዉ መሬቶች የዉሃ ማንጣፈፍ ተግባር ሳይከናወንባቸዉ ተጠብቀዉ ለተፈጥሮ አካባቢና ብዝሀ ህይወት ጥበቃ አገልግሎት መዋል ይገባቸዋል፡፡

2/ በጊዜያዊነት ዉሃ የሚተኛባቸዉ መሬቶች የአካባቢ ተጨባጭ ሁኔታን ግምት ዉስጥ ያስገባ የሶሽዮ-ኢኮኖሚና ባዮ ፊዚካል ጥናት ላይ በተመሰረተ የአሳታፊ መሬት አጠቃቀም ዕቅድ ላይ ለተቀመጠዉ ዓላማ መዋል ይገባቸዋል፡፡

3/ በቋሚነት ዉሃ አዘል በሆኑና የዉሃ አካላት መሬት ላይ የዉሃን መጠን የሚያዛባ ማናቸውንም ተግባር ማከናወን ክልክል ነዉ፡፡

4/ ከዉሃ አዘል መሬቶች ላይ ሳር አጭዶ መጠቀም ይቻላል፡፡

horoonsi'ra dandiinanni.

24. **Dannawu Baatto Horoonsishsha**

1/ Dannawu baattimmanni egennantino mulqantino laalcho uytannokki baatto shoturinni gawajjantara dandiitanno eelallichonna ilaalaame qooxeessubba garunni horoonsi'rate dagate beeqqonni mittimma lata noonsa. Tittirshu wodhotenni gumulamanno.

2/ Dannawu baatto qooxeessu daga beeqqonninna hajo la'annonsi bisinni gumullenna baatto gawajjantannokki garinni hayisso mide horoonsi'rate, dubbo latisate, diishsho ceatenna qulxu'me ceate latishshira hossara dandiitanno.

3/ Konni quwi cinaancho quwi (2) woro noo gedeenni heedheena dannawunnita dubbu baatto wole baattote horoonsishshi widira soorra dandiinannikkiha ikkanna dubbonna dubbunni afi'nanni laalcho horoonsi'ra dandiinanni.

4/ Konni quwi cinaancho quwi (3) woro noo gedeenni heedheena gadachitannonna dagate horora hossanno latishshu xa'mo ikkite Qoqqowu Irshunna Kalaqamu Jiro Latishi Biironni xiinxallote aana kaima asitino fajjo afi'niro loosu aana hossanno.

5/ Looso hooggino weddeli maamaruni tantanante dannawu baatto gutunni horoonsi'rate xa'mo shiqishshuro konni quwi cinaancho quwa (2) aana tittirroonni garinni latisse horoonsidhara yanna bikkine fajjinansara dandiinanni.

25. **Mulqantinonna Gawajjantino Baatto Horoonsishsha**

1/ Ayee eelallicho aana heedhannoti mulqantinonna gawajjantino baatto bandenna qoqqombe mannunna saada kissannokki gede assine woyyaabbanno asinanni. Tittirsha wodhoteni gumullanni.

2/ Mulqantinonna irshaho injiitannokki qoqqomboonni baatto lattukkinni

24. **የወል መሬቶች አጠቃቀም**

1/ በወል ይዞታነት የሚታወቁ የተራቆቱ ምርታማ ያልሆኑ መሬቶች በቀላሉ ሊጎዱ የሚችሉ ተዳፋትና ተራራማ አካባቢዎች በአግባቡ በመጠቀም በኅብረተሰብ ተሳትፎ በጋራ መልማት አለባቸው፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፣

2/ የወል መሬቶች በአካባቢው ኅብረተሰብ ተሳትፎና አግባብ ባለው አካል ተወስኖ መሬቱን በማይጎዳ መልኩ ሳርን አጭዶ ለመጠቀም፣ ለደን ልማት፣ ለንብ እርባታና ለአሳ እርባታ ልማት ሊዉሉ ይችላሉ፡፡

3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ከወል የደን መሬትን ለሌላ የመሬት አጠቃቀም መቀየር የማይቻል ሲሆን ደንና የደን ዉጤቶችን መጠቀም ይቻላል፡፡

4/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌ ቢኖርም አስገዳጅና ለህዝብ ጥቅም የሚዉል የልማት ጥያቄ ሆኖ በክልሉ እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮ በጥናት ላይ የተመሰረተ ፍቃድ ሲገኝ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

5/ ስራ አጥ ወጣቶች በማህበር ተደራጅተው የወል መሬቶችን በጋራ የመጠቀም ጥያቄ ሲያቀርቡ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ላይ በተዘረዘረው መልኩ አልምተው እንዲጠቀሙ በጊዜ ገደብ ሊፈቀድላቸው ይችላል፡፡

25. **የተራቆቱና የተጎዱ መሬቶች አጠቃቀም**

1/ በማንኛዉም ተዳፋት ላይ የሚገኙ የተራቆቱና የተጎዱ መሬቶች ተለይተዉና ተከልለዉ ከሰዉና ከእንስሳት ንኪኪ ነጻ ሆነዉ እንዲያገግሙ ይደረጋል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፤

horonsi'ranna qoronboonni qooxeessa tayse ea hoolloonnite.

3/ Gawajjantino baatto agarantannonna woyyaabbanno ha'rinsho baattote horonsishshi mixo garinni ikka noose.

**Cinaancho Gafa Lame**

26. **Gawajjaancho Baattote Horoonsishshubba Badanna Qorqorsha Assa**

1/ Qoqqowu baattote horoonsishsha lainohunni hajo la'annosi bisi gutamaano bissa qineessatenni bushshaho, waaho, dubboho, hayissote, paarkete, irshunna wole baatto aana assinanni gawajjitanno horoonsishshubbanna loossa xiinxallotenni badanno.

2/ Konni quwira cinaancho quwi (1) garinni gawajjitanno baattote horoonsishsha yine bandoonni loossa hajo la'annosi bisi qorqorsha assanno.

3/ Ayetino baatto babbaxxitino hexxora horoonsidhanno uurrinshubba, gibirinnu investerooti, safote latishshi ijaarsha loossanno bissanna baadiyyete baatto amado annuwi gawajjaancho baattote horonshi loossa qorqortanno bissa ledo halamate gadacho noonsa.

4/ Woradu hajo la'annosi bisi woradu giddo kalaqantannota gawajjaancho baattote horonsishshi loossa badatenna qorqorate gadacho noosi.

5/ Mittu mittunku ollii baattote horonsishshi mixo garinni gawajjaancho baattote

2/ የተራቆቱና ለእርሻ አመቺ ያልሆኑ የተከለሉ መሬቶች ሳያገግሙ መጠቀምና የተከለለዉን አካባቢ ጥሶ መግባት ክልክል ነዉ፡፡

3/ የተጎዱ መሬቶች የሚጠበቁበትና የሚያገግሙበት ሂደት በመሬት አጠቃቀም ዕቅድ መሰረት መሆን አለበት፡፡

**ንዑስ ክፍል ሁለት**

26. **ጎጂ የመሬት አጠቃቀሞችን ስለመለየትና ሰለመቆጣጠር**

1/ በክልሉ የመሬት አጠቃቀምን በተመለከተ አግባብነት ያለዉ አካል ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር በአፈር፣ በዉሃ፣ በደን፣ በግጦሽ፣ በፓርክ፣ በእርሻና ሌሎችም መሬቶች ላይ የሚከናወኑ ጎጂ አጠቃቀሞችንና ተግባራትን በጥናት ይለያል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ጎጂ የመሬት አጠቃቀም ተብለዉ የተለዩ ተግባራትን አግባብነት ያለው አካል ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

3/ ማናቸዉም መሬትን ለተለያዩ ዓላማዎች የሚጠቀሙ ተቋማት፣ የግብርና ኢንቨስተሮች፣ የመሰረተ ልማት ግንባታ የሚያካሂዱ አካላት እና የገጠር መሬት ባለይዞታዎች ጎጂ የመሬት አጠቃቀም ተግባሮችን ከሚቆጣጠሩ አካላት ጋር የመተባበር ግዴታ አለባቸዉ፡፡

4/ የወረዳው አግባብነት ያለዉ አካል በወረዳዉ የሚከሰቱትን ጎጂ የመሬት አጠቃቀም ተግባራትን የመለየትና የመቆጣጠር ግዴታ አለበት፡፡

5/ እያንዳንዱ ቀበሌ በመሬት አጠቃቀም ዕቅድ መሰረት ጎጂ የመሬት አጠቃቀም ተግባራትን መቆጣጠርና ማስቆም አለበት፡፡

horonsishshi loossa qorqoranna uurrisa noosi.

**Cinaancho Gafa Sase**

27. **Baattote Horoonsishshi Aana Tungoonni Ittishsha**

1/ Amadote danni qooxeessira, irshu, caffaame, way burqanno woy eelanno, hayissotenni woy dubbunni diwante agarantino baatto aana woy qooxeessira ayee baarzaafete mu'ronna wole gawajjo iillishshanno mu'ro kaasa hattono gawajjaancho loossa loosa hoolloonnite. Tittirsha wodhotenni gumullanni.

2/ Kuni lallawi loosu aana hosara albaanni kaansoonni baarzaafenna loonsoonni wole gawajjaancho loossa qooxxeessu akati garinni irshu xiinxoranna amadote annuwi danni qooxeessira gawajjo iillishshannoha ikkiro mereersitino baattote horoonsishshinni fultanno wodho garinni hoollanni assinanni.

3/ Eelallichimmase xibbunni 30 anganna hakkuy woro ikkitino baadiyyete baatto horonsi'raano baattote amadooshshi bushshu hoshooshamme ajishannoha ikka noosiha ikkanna qunfete anje noo qooxeessira waa amadate hayyono ha'runsinoha ikka hasiissanno.

4/ Eelallichimmase xibbunni 31 kayse 60 anga ikkitino baadiyyete baatto horoonsi'raano diru gidi latishshira horoonsi'ra dandiitannohu gara ikkitinorenna deerransa agadhitinore bushshunna way agarooshshi tekinolooje loosatenni calla ikkanno.

**ንዑስ ክፍል ሦስት**

27. **በመሬት አጠቃቀም ላይ ስለተጣሉ ገደቦች**

1/ በባለይዞታዎች ድንበር አከባቢ፣ በእርሻ፣ በረግረጋማ፣ ውሃ በሚፈልቅበት ወይም በሚተኛበት፣ በሳር ወይም በደን ተሸፍነዉ በተጠበቁ መሬቶች ላይ ወይም አከባቢ ማንኛውንም የባህር ዛፍ ተክል እና ሌሎች ጉዳት የሚያደርሱ ተክሎችን መትከል እንዲሁም ጎጂ ተግባራትን ማከናወን የተከለከለ ነው፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

2/ ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተተከሉ ባህር ዛፍና የተተገበሩ ሌሎች ጎጂ ተግባራት በአካባቢዉ ተጨባጭ ሁኔታ በእርሻ ማሳ እና በባለይዞታዎች ድንበር አካባቢ ጉዳት የሚያደርሱ ከሆነ በአሳታፊ የመሬት አጠቃቀም በሚወጣ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት እንዲወገድ ይደረጋል፡፡

3/ ተዳፋትነቱ 30 በመቶና ከዚያ በታች የሆኑ የገጠር መሬት ተጠቃሚዎች የመሬት አያያዝ የአፈር ብክለትን የሚቀንስ መሆን ያለበት ሲሆን እርጥበት አጠር አካባቢዎች ውሀን የመያዝ ስልትን የተከተለ መሆን አለበት፡፡

4/ ተዳፋትነቱ ከ31 እስከ 60 በመቶ የሆነ የገጠር መሬትን የሚጠቀሙ ለዓመታዊ ሰብሎች ልማት ማዋል የሚችሉት አግባብነት ያላቸውንና ደረጃቸዉን የጠበቁ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ቴክኖሎጂዎችን በመስራት ብቻ ይሆናል፡፡

5/ ተዳፋትነቱ ከ60 በመቶ በላይ የሆነ የገጠር መሬት ለዓመታዊ ሰብልና ለልቅ ግጦሽ አገልግሎት መዋል የለበትም፡፡ ሆኖም

5/ Eelallichimmase xibbunni 60 ale ikkitino baadiyyete baatto diru gidinna hayisso allaa’late owaantera hosa dinose. Ikeennano haqqete, uurrinshu kaashshira, diishsho ceate, saadate sagale latishshiranna daa”attote horora hossara dandiitanno.

6/ Bobbooddanna gawajjantino baadiyyete baatto qarqaru dagoomi halammenni baattote iima bushshunna way agarooshshe tekinoloojubbanna haqqe kaasate loossa loosatenni wirro lattanno gedenna horote aana hossanno gede assa hasiissanno.

7/ Ayee baadiyyete baatto horoonsi’raanchi ikkado ekistenshiinete owaate afi’ranno woyte woyyaabbinota budunna sayinsaawe baattote horonshinna amadooshshi hayyo horonsi’ratenna irshunna hayissote baatto laalchimma agarate gadacho noosi.

8/ Doogonna wole safote latishshubba ijaarsitanno bissa baattote aana gawajjo iillishannokki garinni loossansa loosa hasiissannonsaha ikkanna baatto gawajjantuha ikkiro iillitino gawajjora qarqaru dagara kiiso baatanna baatto wirro latisate gadacho noonsa.

9/ Baadillitte doogonni kalaqamu shiilo, ijaarsu owaantera hossanno shaafanna kincho labbannore unte fushshatenni horoonsidhanno bissa baattote aana gawajjo iillishannokki garinni loosate gadacho noonsa. Tittirshu wodhotenni gumulamanno.

10/ Ayno baadiyyete baatto horoonsi’raanchi bushshu hoshooshame boonu widira

ለዛፍ፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለንብ ማነብ፣ ለእንስሳት መኖ ልማትና ለቱሪስት መስብነት ሊውል ይችላል፡፡

6/ ቦረቦራማና የተጎዱ የገጠር መሬቶችን በአካባቢው ማህበረሰብ ትብብር ስነ-አካለዊና ሥነ-ሕይወታዊ ስራዎችን በመስራት እንዲያገግሙና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሊደረግ ይገባል፡፡

7/ ማንኛውም የገጠር መሬት ተጠቃሚ በቂ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ሲያገኝ የተሻሻሉ ባህላዊና ሳይንሳዊ የመሬት አጠቃቀምና አያያዝ ዘዴዎችን የመጠቀምና የእርሻና የግጦሽ መሬቶችን ምርታማነት የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

8/ መንገድንና ሌሎች መሰረተ ልማቶችን የሚገነቡ አካላት በመሬት ላይ ጉዳት በማያደርስ አኳኃን ተግባራቸዉን የማከናወን ግዴታ ያለባቸዉ ሲሆን መሬቱ ተጎድቶ ከተገኘ ለደረሰዉ ጥፋት ለአካባቢዉ ህብረተሰብ ካሳ የመክፈልና መሬቱን እንዲያገግም የማድረግ ግዴታ አለባቸዉ፡፡

9/ በባህላዊ መንገድ የተፈጥሮ ማዕድናት፣ ለግንባታ አገልግሎት የሚዉሉ እንደ አሸዋና ድንጋይ የመሳሰሉትን በቁፋሮ እያወጡ የሚገለገሉ አካላት በመሬት ላይ ጉዳት በማያደርስ አኳኃን የማከናወን ግዴታ አለባቸዉ፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

10/ ማንኛዉም የገጠር መሬት ተጠቃሚ አፈሩ ተሸርሽሮ ወደ ገደልነት በተቀየረ አከባቢ በቅርብ ርቀት ላይ የእርሻ ስራ ማከናወን አይችልም፡፡ እንዲሁም የገደላማነት መስፋፋትን የሚከላከሉ ስነ-ህይወታዊና ስነ አካላዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎችን ማከናወን ይኖርበታል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

soorramino qooxeessira muli xeertinyi aana irshu looso loosa didandaanno. Hattono boonna hala’la hooltanno bushshunna way agarooshshe tekinoloojubbanna haqqe kaasate loosso loosa noosi. Tittirshu wodhotenni gumulanno.

11/ Garbuwatenni, laggatenni, kalaqamu dubbinninna baalu ragi horo noonsa batinye lubbuwa jironni bikkamino xeertinye loonsannikki baycho agura hasiissanno. Tittirshu wodhotenni gumulamanno.

12/ Konni quwi cinaancho quwi (11) woro garinni hee’ranno loonsannikki baychi kalaqamu jiro hala’linyi, bikkinninna horo garinni babbaxxannoha ikke qoqqowunni assinanni xiinxallonninna woradu qooxeessu mereersitno baadiyyete baatto horoonsishshi mixo garinni loosamanno.

13/ Hajo la’annonsa bissa baadiyyete baatto aana haaruudde irshu investimente uurrisidhannonna halashshidhanno woyte hattono safote latishshuwa diriirsitanno woyte qooxeessu keeraanchimma hembeeltara dandiitanno qarrubba sayinsete garinni hunate hayyonna loossa mixonsara eessite loosa noonsa.

14/ Gorsu baatto aana quchumu, safarunna owaante uytanno uurrinshubba ijaarsa hattono gawajjanno kaashsho kaasa hoolloonnite.

15/ Aliidinna woriidi way laayyo ragaanni horoonsi’ranno dagoomi mereero taalo ikkitino way horoonsishshi amuraati

11/ ከሀይቆች፣ ከወንዞች፣ ከተፈጥሮ ደኖችና ሁለንተናዊ ጠቀሜታ ካላቸዉ የብዝሀ-ህይወት ሀብቶች በተወሰነ ርቀት ነጻ ክልል መተዉ አለበት፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

12/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (11) በተደነገገው መሰረት የሚኖረው ነጻ ክልል ርቀት እንደ ተፈጥሮ ሀብቱ ስፋት፣ መጠንና ጠቀሜታ የሚለያይ ሆኖ በክልሉ በሚደረጉ ጥናቶችና በወረዳ አካባቢያዊ አሳታፊ የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድ መሰረት ይተገበራል፡፡

13/ የሚመለከታቸው አካላት በገጠር መሬት ላይ አዳዲስ የእርሻ ኢንቨስትመንቶች ሲያቋቋሙና ሲያስፋፉ እንዲሁም የመሰረተ ልማት አውታሮች ሲዘረጉ የአካባቢ ደህንነትን ሊያናጉ የሚችሉ ችግሮች ሳይንሳዊ ማስወገጃ ስልቶችንና ተግባራትን በዕቅዶቻቸው አካተው መተግበር አለባቸው፡፡

14/ በመስኖ መሬቶች ላይ የከተማ፣ የሰፈራና የአገልግሎት ሰጭ ተቋማት ግንባታ እንዲሁም ጎጂ ተክሎችን መትከል የተከለከለ ነው፡፡

15/ በላይኛውና በታችኛው የተፋሰስ ክፍል ባለ ተጠቃሚ ህብረተሰብ መካከል ፍትሃዊ የሆነ የውሃ አጠቃቀም ሥርዓት እንዲኖር መደረግ አለበት፡፡

16/ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች በተከናወነባቸውና በሚከናወንባቸው

hee'ranno gede assa hasiissanno.

16/ Bushshunna way agarooshshi loossa loosantinonna loonsanni hattono uurrinshu kaashsho latinsoonniwanna latinsanniwa ayee dani baaddiyyete baatto aana garimale saadatenni allaa'la hooloonnite. Ikkeennano minde horoonsi'ra dandiinanni.

17/ Dubboho, dubbu saadara, bushshu agarooshshinna latishshira, shiilote latishshiranna xaggete horora qoqqomboonni baatto xaphoomu akatinsa amado ledo hegerera agarama noose.

18/ Dubbu baatto horoonsishsha Lainohunni

a/ Mootimmate woy dannawu dubbi gaangaawira noo baatto loosidhe galtinori dubbu giddo heedhanno haqqete sircho ikkitinokkire dubbu giddo jiro yaano: dubbu buna, koroorima, barbare, hayissonna wolootano sumuummetenni horoonsi'ra dandiitannoha ikkirono dubbo buujjanna yannitte baattote horoonsishsha soorra hoolloonnite.

b/ Mootimmate woy dannawu dubbi gaangaawira heedhanno baadiyyete baatto amado annuwi ayee daninnino dubbu baatto hallanyu amadonsa widira qole qoqqopha hoolloonnite.

c/ Ayee garinnino mootimmatenni woy dannawunni amadantino dubbu baatto baattote horoonsishshi massagaancho mixonni fajja hoongiro wole horora

እንዲሁም ቋሚ ተክሎች በለሙበትና በሚለሙበት በማንኛውም ዓይነት የገጠር መሬት ላይ ልቅ የእንስሳት ግጦሽ የተከለከለ ነው፡፡ ሆኖም አጭዶ መጠቀም ይቻላል፡፡

17/ ለደን፣ ለዱር እንስሳት፣ ለአፈር ጥበቃና ልማት፣ ለማዕድን ልማትና ለታሪካዊ ጠቀሜታ የተከለሉ መሬቶች ከአጠቃላይ ሥነ-ምህዳር ይዞታቸው ጋር በዘላቂነት መጠበቅ አለበት፡፡

18/ የደን መሬቶች አጠቃቀምን በተመለከተ

ሀ/ በመንግሥት ወይም በወል ደን ዙሪያ ያሉ አርሶ አደሮች በደኑ ውስጥ የሚገኙ የዛፍ ዝርያ ያልሆኑ የደን ውስጥ ሀብቶችን ማለትም የጫካ ቡና፣ ኮሮሪማ፣ ሚጥሚጣ፣ ሣርና ሌሎችንም በስምምነት መጠቀም የሚችሉ ቢሆንም ደኑን መጨፍጨፍና ወቅታዊ የመሬት አጠቃቀሙን መቀየር የተከለከለ ነዉ፡፡

ለ/ በመንግስት ወይም በወል ደን ዙሪያ የሚገኙ የገጠር መሬት ባለይዞታዎች በማንኛዉም መልኩ የደን መሬቱን ወደ ግል ይዞታቸዉ ማካለል የተከለከለ ነዉ፡፡

ሐ/ በማንኛውም ሁኔታ በመንግሥት ወይም በወል የተያዙ የደን መሬቶች በመሬት አጠቃቀም መሪ ዕቅድ ካልተፈቀደ በስተቀር ለሌላ አገልግሎት ማዋል የተከለከለ ነዉ፡፡

19/ ማንኛውም ተጠቃሚ መሬቱን በሕግ ለተከለከለ ተግባር መጠቀም አይችልም፡፡

hosiisa hoolloonnite.

19/ Ayee horoonsi’raanchi baattosi seerunni hoolloonni hajora horoonsi’ra didandaanno.

**Cinaancho Gafa Shoole**

**Baadiyyete Baatto Taje Amuraate Diriirsa**

28. **Baadiyyete Baatto Taje Gamba Assanna Tantana**

1/ Baadiyyete baatto bikka, maareekka, baattote jironna baattote horonshi mixo tajubba hajo la’annosi bisinni woradaho, zoonetenna qoqqowu deerrinni gamba yaanna tanatanama noosi.

2/ Tantanantinoti baattote taje hajo la’annosi bisira sa’’a noose.

29. **Baadiyyete Baatto Taje Maareekko Qixxeessa**

1/ Gobboommu deerrinni uurrrinsannihu baadiyyete baatto taje maareekko ledo xaadannoha qoqqowu baattote taje maareekko uurrinsanni.

2/ Tantanantino baattote bikki, maareekko, amado buuxisiisanna mereersitino baattote horonshi mixo tajubba woradu deerrinni uurrinsanni tajete maarekkora e’anno gede assinanni.

3/ Qoqqowu deerrinni qixxeessinanniti massagaancho baattote horonshi mixo taje qoqqowu tajete maareekko giddora e’anno gede assinanni.

4/ Woradu deerrinni tajete maareekko giddora e’ino taje taashshate biilonyi noosihu woradu Irshunna Kalaqamu Jiro Latishshi Borro Mine ikkanno. Ikkollana tajubba

**ንዑስ ክፍል አራት**

**የገጠር መሬት መረጃ ስርዓት ስለመዘርጋት**

28. **የገጠር መሬት መረጃ ስለማሰባሰብና ስለማደራጀት**

1/ የገጠር መሬት ቅየሳ፣ ምዝገባ፣ የመሬት ሀብቶችና የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ መረጃዎች አግባብ ባለው አካል በወረዳ፣ በዞንና በክልል ደረጃ መሰብሰብና መደራጀት አለበት፡፡

2/ የተደራጀዉ የመሬት መረጃ ለሚመለከተው አካል መተላለፍ ይኖርበታል፡፡

29. **የገጠር መሬት መረጃ ቋት ስለማቋቋም**

1/ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከሚቋቋመው የገጠር መሬት መረጃ ቋትጋር የሚናበብ ክልላዊ የመሬት መረጃ ቋት ይቋቋማል፡፡

2/ የተደራጀ የመሬት ቅየሳ፣ ምዝገባ፣ ይዞታ ማረጋገጥና የአሳታፊ መሬት አጠቃቀም ዕቅድ መረጃ በወረዳ ደረጃ በሚቋቋመዉ የመረጃ ቋት እንዲገባ ይደረጋል፡፡

3/ በክልል ደረጃ የሚዘጋጀዉ መሪ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ መረጃ በክልሉ የመረጃ ቋት ዉስጥ እንዲገባ ይደረጋል፡፡

4/ በወረዳ ደረጃ ወደ መረጃ ቋት ዉስጥ የገባዉን መረጃ የማስተካከል ስልጣን ያለዉ የወረዳዉ የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ጽሕፈት ቤት ይሆናል፡፡ ሆኖም መረጃዎቹ ክልላዊ የፍትህና የልማት

qoqqowunnita farcotenna latishshu hajubba ikkituro Qoqqowu Irshunna Kalaqamu Jiro Latishshi Biiro taje taashsha dandiitanno.

5/ Deerru deerrunkunni tantanantanno taje isilaanchimma agarantinota, xaaddinnonna qinaabbinota ikka noose.

6/ Woradu aleenni noo hajo la'annonsa bissa tajete amado soorritukkinni rippoortete qixxaaworanna tajete fattalara horonsidhara dandiitanno.

30. **Baadiyyete Baatto Taje Tuqishsha**

1/ Ayno baadiyete baatto amado anni xiinxosi lainohunni taje afi'ra dandaanno gede fano assa hasiissanno.

2/ Ayeetano baattote amado anni xiinxo bikkine buuxaminoha baatto leellishanno kaarta uynara albaanni tajete garimma buuxate wo'ma taje hajo la'annosi bisi dagate fano asse hedo uytanno gede assa noosi.

3/ Tajete maareekkora tantanantinoti baattote taje xa'miniro hajo la'annosi bisi fajjiro calla xa'mirino bisira iillitanno assinanni.

4/ Baattote maareekkonni taje afidhino bissa taje sayikki bisira saysa didandiitanno.

31. **Baattote Taje Yannitte Assa**

1/ Baattote amadonni horonsi'rate qoosso aana ayee soorro assiniro taje yannite assa hasiissanno.

2/ Amadote anninna xiinxote hala'la woy ajate korkaatinni dagganno soorro heedhuro kaadasiterete bikki taje yannitte assa hasiissanno.

ጉዳዮች ከሆኑ የክልሉ እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ መረጃውን ማስተካከል ይችላል፡፡

5/ በየደረጃዉ የሚደራጀዉ መረጃ ጥራቱን የጠበቀ፣ ተናባቢና የተቀናጀ መሆን አለበት፡፡

6/ ከወረዳ በላይ ያሉ አግባብነት ያላቸው አካላት የመረጃዉን ይዘት ሳይቀይሩ ለሪፖርት ዝግጅትና ለመረጃ ትንተና ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡

30. **የገጠር መሬት መረጃ ተደራሽ ስለማድረግ**

1/ ማንኛውም የገጠር መሬት ባለይዞታ ማሳውን በተመለከተ መረጃ ማግኘት እንዲችል ክፍት መደረግ አለበት፡፡

2/ የማንኛውም ባለይዞታ ማሳ ተለክቶ የይዞታ ማረጋገጫ ማሳ ጠቋሚ ካርታ ከመሰጠቱ በፊት የመረጃውን ትክክለኛነት ለማጣራት ሙሉ መረጃው አግባብነት ያለው አካል ለህዝብ ክፍት አድርጎ ማስተቸት አለበት፡፡

3/ በመረጃ ቋት የተደራጀው የመሬት መረጃ ሲጠየቅ አግባብነት ባለው አካል ሲፈቅድ ብቻ ለጠያቂው አካል ተደራሽ ይደረጋል፡፡

4/ ከመሬት መረጃ ቋት መረጃውን ያገኙ አካላት መረጃውን ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ አይችሉም፡፡

31.**የመሬት መረጃን ወቅታዊ ስለማድረግ**

1/ በመሬት ይዞታ የመጠቀም መብት ላይ ማንኛውም ለውጥ ሲደረግ መረጃው ወቅታዊ መደረግ አለበት፡፡

2/ የባለይዞታና በማሳ መስፋት ወይም ማነስ ምክንያት የሚመጣ ለውጥ ሲኖር የካዳስተር ቅየሳው መረጃ ወቅታዊ መደረግ አለበት፡፡

3/ የአሳታፊ መሬት አጠቃቀም ዕቅድ መረጃዎች በህብረተሰቡ ጥያቄ ቀርቦ በዕቅዱ ላይ ለውጥ ሲደረግበት መረጃዉ

3/ Mereersitino baattote horonshi mixo tajubba dagate xa'monni shiqqeenna mixote aana soorro assiniro taje yannitte assa hasiissanno.

### Cinaancho Gafa Onte
### Baadiyyete Baatto Aana Ka'anno Yekkeero Tirranni Gara

32. **Baadiyyete Baatto Yekkeero Tira**

1/ Baadiyyete baatto amado qoosso ledo amadaminohunni yekkeero ka'uro ku'laato balaxxe olluu baattote gashshootinna horonsishshu komitera shiqa noose.

2/ Woxaratto shiqqinonsa baattote gashshooti komite woxaratto shiqqu barra lamunku widi araaru cimeeyye doodhitanno gede assite doorantino cimeeyyeno hajo buuxxe 14 barri giddo uytinota gumulote hedo komitete uytu barra lamunku widira borrotenni uynanni.

3/ Araaru cimeeyye uytino gumulote hedonni sumuu yiinokkihu hajosi Woradu Yoo Minira shiqishi'ra dandaanno.

4/ Konni quwira cinaancho quwa 3 aana worroonnihu noo gede hee'reenna baadiyyete baatto amadonna horonsi'rate qoosso lainohunni ka'anno yekkeero shiqisi'rate amanyooti yoote mini lallawira worroonni garinni ikkanno.

5/ Baadiyyete baatto amadonna horonsi'rate qoosso lainohunni ka'anno yekkeero gashshootu hajubba ikkituro hajo la'annonsa bissa gobbanni wolu ayee bisinni la"antara didandiitanno.

### Cinaancho Gafa Lee
### Baadiyyete Baatto Horoonsi'raano Gadachonna Gashshootu Qaafo

33. **Baadiyyete Baatto Horoonsi'raano Gadacho**

1/ Ayno baadiyyete baatto amado anni baatto

ወቅታዊ መደረግ አለበት፡፡

### ንዑስ ክፍል አምስት
### በገጠር መሬት ላይ የሚነሱ ክርክሮች አፈታት

32. **የገጠር መሬት ክርክር አፈታት**

1/ ከገጠር መሬት ይዞታ መብት ጋር በተያያዘ ክርክር ሲነሳ ማመልከቻ በመጀመሪያ ለቀበሌው መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ መቅረብ አለበት፡፡

2/ አቤቱታ የቀረበለት የመሬት አስተዳደር ኮሚቴ አቤቱታዉ በቀረበለት ቀን ሁለቱም ወገኖች አስማሚ ሽማግሌዎች እንዲመርጡ ያደርግና የተመረጡ ሽማግሌዎች ጉዳዩን አጣርተው በ14 ቀን ዉስጥ የሰጡትን የውሳኔ ሀሳብ ለኮሚቴው ባቀረቡለት ቀን ለሁለቱም ወገኖች በጽሁፍ ይሰጣል፡፡

3/ አስማሚ ሽማግሌዎች በሚሰጡት የዉሳኔ ሃሳብ ያልተስማማ ወገን ጉዳዩን ለወረዳ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ የተገለጸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የገጠር መሬት ይዞታና አጠቃቀም መብትን በተመለከተ የሚነሱ ክርክሮች አቀራረብ ሥነ ሥርዓት በፍርድ ቤቶች አዋጅ ላይ በተቀመጠዉ መሠረት ይሆናል፡፡

5/ በገጠር መሬት ይዞታና የመጠቀም መብትን አስመልክቶ የሚነሱ ክርክሮች አስተዳደራዊ ጉዳዮች ከሆኑ አግባብነት ካላቸዉ አካላት ዉጪ በሌላ ማናቸዉም አካል ሊታዩ አይችሉም፡፡

### ንዑስ ክፍል ስድስት
### የገጠር መሬት ተጠቃሚዎች ግዴታና አስተዳደራዊ እርምጃዎች

33. **የገጠር መሬት ተጠቃሚዎች ግዴታ**

1/ ማንኛውም የገጠር መሬት ባለይዞታ መሬቱ አግባብ ባለው አካል የምዝገባና የቅየሣ ሥራ

hajo la’annosi bisinni maareekkatenna bikkisiisate looso ha’risate xa’miniro halamate gadacho noosi.

2/ Ayno baadiyyete baatto amado anni baattosi garunni horoonsi’ratenna gargarate gadacho noosi.

3/ Gorsu gadawenna wolootu safote latishshi ijaarsa diriisinanni yannara amadote anni baatto aananni sa’annoha ikkiro fajjate gadacho noosi. Tittirisha wodhotenni gumullanni.

4/ Ayno baattote amado anni horoonsi’rate qoossosi fajjosinni aguriro aguri barrinni hanafe heedhanno 60 barrubba giddo egensiisatenna amadote buuxxishsha leellishshanno kaarta hajo la’annosi bisira qola noosi.

5/ Hallanyootu, mootimmaamenna, mootimmaame ikkitinokki uurrinshubba baattotenni horonsi’rate shiqishidhanno latishshu mixo qooxeessu keeraanchimma hembeeltannokkita ikkase hajo la’annosi bisinni buuxama noosi.

6/ Safote latishshi ijaarsha ha’rissanno bissa baatto horonsidhanno woyte qooxeessu keeranchimma gawajjite leelturo konni lallawininna gara ikkino seerinni xa’mantannoha ikke qooxeessa noowa qolate gadacho noonsa.

7/ Ayee hallanyino ikko uurinsha kirunni adhitino baatto aana gara ikkitino baattote amadooshshi loossa kiru yannansanni loosu aana hosiisate yawonna gadacho noonsa. Hattono kiru yanna gooffuro woy sheemaatu

እንዲካሄድ ሲጠየቅ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

2/ ማንኛውም የገጠር መሬት ባለይዞታ መሬቱን በአግባቡ የመጠቀምና የመንከባከብ ግዴታ አለበት፡፡

3/ የመስኖ ቦዮችና ሌሎች የመሠረተ ልማት አውታሮች በሚዘረጉበት ወቅት በባለይዞታው መሬት ላይ የሚያልፉ ከሆነ ይህንኑ የመፍቀድ ግዴታ አለበት፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

4/ ማንኛውም ባለይዞታ የመጠቀም መብቱን በፈቃዱ ሲተው ከተወበት ቀን ጀምሮ ባሉት 60 ቀናት ውስጥ የማሳወቅ እና የይዞታ ማረጋገጫ የማሳ ጠቋሚ ካርታውንም አግባብነት ላለው አካል መመለስ አለበት፡፡

5/ ግለሰቦች፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በመሬት ለመጠቀም የሚያቀርቡት የልማት ዕቅድ የአካባቢ ደህንነትን የማያናጋ መሆኑን አግባብ በሆነ አካል መረጋገጥ አለበት፡፡

6/ የመሰረተ ልማት ግንባታ የሚያካሂዱ አካላት መሬቱን ሲጠቀሙ የአካባቢውን ደህንነት ጉድተው ከተገኙ በዚህ አዋጅና አግባብ ባለው ሕግ የሚጠየቁ ሆኖ አካባቢውን ወደ ነበረበት ሁኔታ የመመለስ ግዴታ አለባቸው፡፡

7/ ማንኛውም ግለሰብም ሆነ ድርጅት በተከራየው መሬት ላይ አግባብ ያለው የመሬት አያያዝ ሥራዎችን በኪራይ ዘመኑ ተግባራዊ የማድረግ ኃላፊነትና ግዴታ አለበት፡፡ እንዲሁም የኪራይ ዘመን ሲያበቃ ወይንም ውሉ ሲቋረጥ የመሬቱ የተፈጥሮ ይዘት እንደተጠበቀ ለአከራዩ የመመለስ ግዴታ አለበት፡፡

8/ ማንኛውም የገጠር መሬት ተጠቃሚ መሬቱን በመሬት አጠቃቀም ዕቅድ መሠረት ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

9/ ማንኛውም የወል መሬት ተጠቃሚ በመሬቱ ላይ ያለውን ሀብት በአግባቡ የመያዝና የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

10/ ማንኛውም ግለሰብም ሆነ ድርጅት መሬቱን ከተፈቀደለት አላማ ውጪ መጠቀም አይችልም፡፡

11/ የገጠር መሬት ተጠቃሚው የመሬትና የተፈጥሮ ሀብት መልካም አያያዝን

uurriro baattote kalaqamu amadose agarantino gedeenni heedheenanni kira uyhura qolate gadacho noonsa.

8/ Ayno baadiyyete baatto horoonsi’raanchi baattote horonsishshi mixo garinni loosu aana hosiisate gadacho noosi.

9/ Ayno dannawu baatto amado horoonsi’raanchi baattote aana noo jiro garunni amadatenna agarate gadacho noosi.

10/ Ayee hallanyino ikko uurrinsha baattosi fajjinoonnisi hexxo gobbaanni horoonsi’ra didandaanno.

11/ Baadiyyete baatto horoonsi’raanchi baattotenna kalaqamu jiro dancha amadooshshe lainohunni qasiisote amadote anni ledo halame loosate gadacho noosi.

12/ Baadiyyete baatto mootimmate wiinni investimeentetenni afidhe horonsidhannori sheematu yanna gooffuro woy sheematu uurriro baattote kalaqamu amado agarantino garinni mootimmate qolate gadacho noonsa.

13/ Ayno baadiyyete baatto horoonsi’raanchi seerunni uynoonnsi amado horoonsi’rate qoosso gobbaanni halashshe amadanna dannansa qoqqomboonni baatto danna xiiwanna hattono baxxite egenantino doogga cufa hoollonnite.

14/ Ayeetano way bisi baatto horoonsi’ranno hallanyi woy uurrinsha waa daaffanno, isilaanchimmasi ajishshannonna way giddo heedhanno qulxu’menna woloota batinye lubbo noonsa jiro geeshsha ajishanno garinni horonsi’ra hoollonnite.

15/ Irshunni lata dandiitanno baatto aana aye dani baarzaafete mu’ronna wole gawajjo iillishshanno mu’ro kaasa hattono gawajjaancho loossa loosa hoolloonnite.

16/ Ayee manchi konni quwi cinaancho quwi 15 aana seerroonniha sa”atenni baarzaafete

በተመለከተ ከኩታ ገጠሙ ባለይዞታ ጋር ተባብሮ የመስራት ግዴታ አለበት፡፡

12/ የገጠር መሬትን ከመንግስት በኢንቨስትመንት አግኝተው የሚጠቀሙ የውል ዘመኑ ሲያበቃ ወይንም ውሉ ሲቋረጥ የመሬቱ የተፈጥሮ ይዘት እንደተጠበቀ ለመንግስት የመመለስ ግዴታ አለባቸው፡፡

13/ ማንኛዉም የገጠር መሬት ተጠቃሚ በህግ ከተሰጠዉ የይዞታና የመጠቀም መብት ዉጭ አስፋፍቶ መያዝና ወሰናቸው የተከለለ መሬቶችን ድንበር መግፋትና እንዲሁም ተለይተው የሚታወቁ መንገዶችን መዝጋት ክልክል ነዉ፡፡

14/ ማንኛዉም የዉሃ አካል መሬት ተጠቃሚ ግለሰብ ወይም ድርጅት ዉሃዉን በሚበክል፣ ጥራቱን በሚቀንስና በዉሃ ዉስጥ የሚገኙ ዓሳዎችንና ሌሎች ብዝሃ ህይወታዊ ሀብቶች መጠን በሚቀንስ መልኩ መጠቀም ክልክል ነዉ፡፡

15/ በእርሻ ሊለማ በሚችለዉ መሬት ላይ ማንኛውንም ዓይነት የባህር ዛፍ ተክል እና ሌሎች ጉዳት የሚያደርሱ ተክሎችን መትከል እንዲሁም ጎጂ ተግባራትን ማከናወን የተከለከለ ነው፡፡

16/ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 15 የተደነገገውን በመተላለፍ የባህር ዛፍ ተክል እና ሌሎች ጉዳት የሚያደርሱ ተክሎችን የተከለ እንዲሁም ጎጂ ተግባራትን ያከናወነ እንደሆነ በቀበሌ አስተዳደር ግብርና ጽሕፈት ቤት በኩል ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡(ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል)፡፡

17/ ማንኛዉም የመሬቱ ተጠቃሚ በይዞታዉ ወይም ከይዞታዉ ዉጪ በመንግስት፣ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችና በህብረተሰቡ የተገነቡትን የአፈርና ዉሃ ጥበቃ ህዳጎችን ማፍረስ ክልክል ነዉ፡፡

18/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 17 የተደነገገውን በመተላለፍ የአፈርና ዉሃ ጥበቃ ህዳጎችን ያፈረሰ እንደገና እንዲሰራቸዉ በቀበሌ አስተዳደር ግብርና ጽሕፈት ቤት በኩል ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡

mu'ronna wole gawajjo iillishshanno mu'ro kaasinohu hattono gawajjaancho looso loosinoha ikkiro olluu gashshooti gibirinnu borro mini widoonni qorowishsha uynannisi.(Tittirsha wodhotenni gumullanni)

17/ Ayno baattote horoonsi'raanchi amadosi woy amadosi gobbaanni mootimmate, mootimmaame ikkitinokki uurrinshanna dagoomu beeqqonni loosantino bushshunna way agarooshshi irkanna diiga hoollonnite.

18/ Konni quwi cinaancho quwi 17 aana seerroonniha sa"atenni bushshunna way agarooshshi irkanna diiginohu galagale loosanno gede olluu gashshooti giwirinnu borro mini widoonni qorowishsha uynannisi.

## Gafa Lamala

## Addi Addi Woro

34. **Qoricha.**

1/ Ayee manchi konne lallawa woy lallawa jefisiisate fultino wodhonna biddissubbaa sae leelliro gara ikkino seerinni qorichamanno.

2/ Baattote amadosi haja la'annonsa bissanni maareekisiisikkinni kira uynohu woy konni lallawira worroonni yanna gobbaanni haaronsiisikkinni kiraho uynohu woy kira adhinohu sasu agani geeshsha iillanno shota usura woy 1000 Birra qorichamanno.Kiru sheemaatino digaminoha ikkanno.

3/ Ayee manchi konni lallawi garinni xawinsoonni mini maate gobbaanni baattosi eltotenni saysinoha ikkiro elto diigantanno.

4/ Konni lallawi quwa (33) cinaancho quwa (18) garinni uynoonnisi qorowishshinni taashsho assinokkihu baattote horoonsi'raanchi

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

34. **የቅጣት**

1/ ማንኛውም ሰው ይህን አዋጅ ወይም አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ጥሶ ሲገኝ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ይቀጣል::

2/ የመሬት ይዞታውን በተገቢዉ አካል ሳያስመዘግብ ያከራየ ወይም በዚህ አዋጅ ከተደነገገው የጊዜ ገደብ ውጪ ዕድሳት ሳይደረግ ያከራየ ወይም የተከራየ እስከ ሶስት ወር የሚደርስ ቀላል እስራት ወይም በብር 1,000 ይቀጣል፡፡የኪራይ ዉሉም ፈራሽ ይሆናል፡፡

3/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሰረት ከተዘረዘሩ የቤተሰብ አባላት ዉጪ መሬቱን በስጦታ ያስተላለፈ እንደሆነ ስጦታዉ ፈራሽ ይሆናል፡፡

4/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ (33) ንዑስ አንቀጽ (18) በተደነገገዉ መሰረት በተሰጠው ማስጠንቀቂያ ማስተካከያ ያላደረገ የመሬቱ ተጠቃሚ በይዞታዉ ወይም ከይዞታዉ ዉጪ በመንግስት፣ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችና በህብረተሰቡ የተገነቡትን የአፈርና ዉሃ ጥበቃ ህዳጎችን ያፈረሰ እስከ ሶስት ወር በሚደርስ ቀላል እስራት ወይም ከብር 500 እስከ 1500 ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡ እንዲሁም ያፈረሰውን መልሶ እንዲሰራ ይደረጋል፡፡

5/ የወልና የመንግስት መሬትን በህገ ወጥ መንገድ ያከፋፈለ፣ የይዞታ ማረጋገጫ ጠቋሚ የማሳ ካርታ ያለአግባብ የሰጠ፣ እንደ ማስረጃ ያቀረበ እንደአግባብነቱ በወንጀል

amadosi woy amadosi gobbaanni mootimmate, mootimmaame ikkitinokki uurrinshubbanninna dagoomittetenni loosantinota bushshunna way agarooshshe irkanna diiginohu 3 agani geeshsha iillanno shotu usurinni woy 500 kayse 1500 birra iillanno woxu qorichinni qorichamanno. Hattono diiginoha galagale loosanno gede assinanni.

5/ Dannawunna mootimmate amado seerimale doogonni beehinohu, xiinxo leellishanno kaarta garimala uynohu; tajete gede shiqishi'rihu jaddote seeri roore qorichishannoha ikka hoogiro 1 diro ikkanno usurinninna 10000 Birrinni kayse 20000 Birra qorichamanno. Baattono albaanni noo amado widira higganno.

6/ Dannuwunna mootimmate baatto seerimale doogonni amadinohu woy halashshi'rinohu, xiinxo leellishanno kaarta garimale adhinohu, jaddote seeri roore qorichishannoha ikka hoogiro 6 agani geeshsha ikkanno usurinninna 5000 Birra qorichamanno. Baattono albaanni noo amado widira higganno.

35. **Qoqqowu Irshshunna Kalaqamu Jiro Latishshi Biiro Yawo**

1/ Haja la'annonsa bissa qineessatenni hasiissanno ogimmate irko aatenni konne lallawa jeefisiisate yawo noose.

2/ Zoonetenna woradu deerrinni yanna yannantenni ha'runsotenna keenotenni afi'noonni taje kaima assatenni haaro hedubba burqitannonna hasiisannoha ikkiro loosu aana noo lallawi yanna yannantenni woyaawanno gede assitanno.

ህግ እና በሌሎች ህጎች የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር ከአንድ አመት እስከ ሦስት አመት በሚደርስ እስራት እና ከብር 10,000 እስከ 20,000 ብር የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡ መሬቱም ቀድሞ ወደ ነበረበት ይዞታ ይመለሳል፡፡

6/ የወልና የመንግስት መሬትን በህገ ወጥ መንገድ የያዘ ወይም ያስፋፋ፣ የይዞታ ማረጋገጫ የማሳ ጠቋሚ ካርታ ያለአግባብ የተቀበለ፣ በወንጀል ህግ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር ከስድስት ወር እስከ አንድ አመት በሚደርስ እስራት እና 5000 ብር የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡ መሬቱም ቀድሞ ወደ ነበረበት ይዞታ ይመለሳል፡፡

35. **የክልል እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ ኃላፊነት**

1/ አግባብ ያላቸውን አካላት በማስተባበርና አስፈላጊውን የሙያ ድጋፍ በመስጠት ይህን አዋጅ የማስፈጸም ኃላፊነት አለበት፡፡

2/ በዞንና ወረዳ ደረጃ የተሰባሰቡና በየጊዜው በክትትልና በግምግማ የሚገኙ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ አዳዲስ ሀሣቦች እንዲነደፉና አስፈላጊም ሲሆን በሥራ ላይ ያለው አዋጅ በየጊዜው እንዲሻሻል ያደርጋል፡፡

3/ በፌዴራልና በክልል እንዲሁም በዞኖችና ወረዳዎች መካከል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መረጃ ልውውጥ ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፡፡

4/ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሥርዓትን የሚያስፈጽሙ ተቋሞች በተዋረድ እንዲቋቋሙና የተቋቋሙትም እንዲጠናከሩ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

5/ በቀበሌ ደረጃ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ የማዋቀር ኃላፊነት አለበት፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

3/ Federaaletenna qoqqowu hattono zoonetenna woradu mereero baadiyyete baattote gashshootinna horoonsishshi tajete soorro amuraate hee'ranno gede assitanno.

4/ Baadiyete baatto gashshootinna horoonsishshi amuraate jeefisiissanno uurrinshubba deerru deerrunkunni uurritanno gedenna uurritinorino jawaattanno gede assate yawo noose.

5/ Olluu deerrinni baadiyyete baattote gashshootinna horoonsishshi komite uurrisate yawo noose. Tittirsha wodhotenni gumullanni.

36. **Halamate Gadacho**

Ayee manchi konne lallawa jeefisiisate haja la'annonsa bissa ledo halamate gadacho noosi.

37. **Fitaabeerete Seeri Garimma**

Konni lallawira hanqafantinokkiti baatto labbanno hajubba aana fitaabeerete seeri hasiishshu garinni jeefamannoha ikkanno.

38. **Lallawaho Wolootu Baattonnire Labbanno Seerubba Ledo Hee'rannosi Xaadooshshi**

Baattote jiro ikkitinori dubbu, way, batinyi-lubbo, irshu, shiilote, saada alaallanni baattonna wolootuno qoqqowu deerrinni fultanno seerubba konni lallawi ledo xaaddannore ikka noonsa.

39. **Loosu Aana Hossannokki Seerubba**

Konni lallawi ledo kiphi yaannohu ayee seeri, wodho, biddissu woy rosamino rosichi konni lallawira worroonni hajubba lainohunni jeefishshu dihee'rannonsa.

40. **Wodhonna Biddissa Fushshate Billoonye**

1/ Qoqqowu Gashooti Amaalete Mini konne lallawa jeefisiisate kaa'litanno wodho fushshate dandaanno.

2/ Biiro konni lallawinna lallawa ha'runsite fultanno wodho garinni biddissa fushsha dandiitanno.

41. **Reekkote Seera**

1/ Konni seeri woro kuni lallawi kaajjara

36. **የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

37. **የፍትሐብሔር ሕጉ አግባብነት**

በዚህ አዋጅ ባልተሸፈኑ መሬት ነክ ጉዳዮች ላይ የፍትሐብሔር ሕግ እንደ አግባብነቱ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

38. **አዋጁ ከሌሎች መሬት ነክ ህጎች ጋር ስለሚኖረዉ ግንኙነት**

የመሬት ሀብት በሆኑት በደን፣ በዉሃ፣ በብዝሃ ህይወት፣ በእርሻ፣ በማዕድን፣ በግጦሽና በሌሎችም በክልል ደረጃ የሚወጡ ህጎች ከዚህ አዋጅ ጋር የተናበቡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

39. **ስለተሻሩና ተፈጻሚ ስለማይሆኑ ሕጎች**

ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን ጉዳዮች በተመለከተ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

40. **ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

1/ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚረዳ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

2/ ቢሮዉ በዚህ አዋጅና አዋጁን ተከትሎ በሚወጣው ደንብ መሠረት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

41. **የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

1/ የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች ይህ አዋጅ ከመጽደቁ በፊት በተለያየ ደረጃ የዳኝነት አካላት ፊት ቀርበዉ ክርክር እየተደረገባቸው ባሉ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

albaanni addi addi deerrinni yoo aate bissa albaanni shiqqeenna yekkeero assinanni hee’noonni hajubba aana dijeefisantanno.

2/ Addi addi tekinooloje horonsi’ratenni kuni lallawi fulara albaanni uynoonniti amadote buuxishshi tajete woraqatta loossanno.

42. **Lallawu Loosu Aana Hosanna Yanna**

Kuni lallawi Badheessa 12/2015 M.D hanafe loosu aana hosanno.

**Hawaasa, Badheessa 12/2015 M.D.**

**Desta Ledamo**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Pirezidanticha**

2/ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የተሰጡ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቶች ተቀባይነት አላቸው፡፡

42. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከመጋቢት ፲፪ ቀን ፳፻፲፭ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ሀዋሳ፣ መጋቢት ፲፪ ቀን ፳፻፲፭ ዓ.ም**

**ደስታ ሌዳሞ**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር**